# ጥላ TILA

ጥላ /ህዳር-ታህሳስ 2006 ዓ.ም ሁለተኛ ዓመት ቁ.8 Tila Nov/Dec 2013 2nd year 8th edition


## መንግስት- ስደት—ውርደት





ጥላ
TILA
TILA February 2012 First Year 1st Edition
ወያኔን ያናጋው የአንካ ውሳኔ!!
Harassment tool – Ethiopian anti Terrorism Law
ዛምቢያ—የአፍሪካ ዋንጫ ንጉስ



ጥላ
TILA
TILA May 2012 First Year 2nd Edition
በፖለቲካችን ሁሉም አትሌት መሆን ነው ያለበት!!
አዲዎስ ሮሜሲ!
No More Joseph Konys!!
uefa champions league finale


ጥላ
TILA
TILA August 2012 First Year 3rd Edition
Where is The Ethiopian Prime Minister? WANTED!
The Sugar Candy Mountain



ጥላ
TILA
TILA November 2012 First Year 4th Edition
ሰው ጥራ ቢሉት ራሱ መጣ !
We need a regime change not……
funny but true


ጥላ
TILA
TILA January 2013 1st Year 5th Spe. Edition
በኢ.ህአዴግ ውስጥ የተፈጠረውን ክፍተት ልንጠቀምበት ይገባል።
አቶ ግደይ ዘርዓፅዮን
An opposition member has no right to speak; while
An EPRDF member has no right to think.
CONFEDERATION AFRICAINE DE FOOTBALL CAF


ጥላ
TILA
TILA May 2013 2nd Year 6th Edition
የኢትዮጵያ ፕሬስ ነፃነት ተምሳሌት ርዕዮት ዓለሙ
Free


ጥላ
TILA
TILA August 2013 2nd Year 7th Edition
አባይ ሊያለማን ወይስ ሊያጠፋን?
Mesfin Abraha
An der Obergeis 1
36251 Bad Hersfeld


Those who make peaceful revolution impossible will make violent revolution inevitable
-JFK


The world's ten hungriest countries
1 Burundi 38.8
2 Eritrea 35.0
3 Comoros 33.6
4 Timor-Leste 29.6
5 Sudan (former) 27.0
6 Chad 26.9
7 Yemen, Rep. 26.5
8 Ethiopia 25.7
9 Madagascar 25.2
10 Zambia 24.1
Key
Extremely alarming
Alarming
CONCERN worldwide

# ጥላ


ዋና ስራ አስኪያጅ — General Manager

መስፍን አብርሃ — Mesfin Abraha

## ዋና አዘጋጆች — Editor In Chiefs

እየሩሳሌም ሱሞሮ — Eyerusalem Sumoro
ዳዊት ፋንታ — Dawit Fanta
ደሳለኝ አበበው — Desalegne Abebew

## አዘጋጆች — Editors

ዮሃንስ ሳምሶን — Yohanes Samson
ደበበ ከበደ — Debebe Kebede
ፍስሃፅዮን ሃይለገብርኤል — Fisshatsion Hailegeberile

## ጽሁፍ አስተባባሪዎች — Coordinators

ብርሃኑ ባዩ — Berhanu Baue
ኤደን ዳዊት — Eden Dawit
አስናቀች ጥላሁን — Asnakch Telahun
በተወዳጅ አድነው — Betewedaj Adenew

## የኮምፒዩተር ፅሁፍ ቅንብር — Computer Graphics

ህሊና ዳዊት — Hilina Dawit



የጥላ መጽሔት አድራሻ/Tila Magazine Address
Mesfin Abraha
An der Obergeis 1
36251 Bad Hersfeld
Email:- tilamagazine@yahoo.de
Web-Site:- tilamagazine.yolasite.com
Tel.No.:- 015222195567, 017659384456, 017671668780

# ማውጫ


የፈጠራ ባለቤቱ በጀርመን 7

ስደት እስከመቼ 8

መሄጃ ያጣ ትውልድ

ለሳኡዲው ግፍ ተጠያቂው ማነው?

ባርነት እስከ የት? 10

አገራችንን እንታደጋት 10

ህልመኞቹ ማናቸው? 10

የስደት ውርደት በዛ... 11

ውሃን ለቅጣት መሳሪያነት 12

ድር ቢያብር.... 13

አ ሚሊኒየም ወያኔ... 13

ተጠያቂው ማነው? 14

መንግስታችንን በአይሲሲ ፊት

ለምን ተዋረድን? 15

ወንድሜ ሆይ አንሳኝ- ግጥም

እውን ኬኔዲን ማን ገደላቸው?-

ፍንጭ ጠቋሚ ሐተታ/ ከጥላ መጽሔት 18

መንግስትም በሳኡዲው ግፍ ይጠየቃል

በኢትዮጵያ መንግስት አለ ወይ?

Political cartoon

Reconciliation 21

The devastating HR....21

Saudi Arabia Govt. 22

Saudi vs Human Right 23

Ending the Silence 24

Demonstration is a .... 24

Oromos are still... 24


መልካም ንባብ

ጥላ መጽሔት



# ABOUT TILA

Realizing the fact that the digital age has empowered and made ordinary people across the world irrepressible beyond their imagination, **WE** aims to serve as a credible platform that will spread uncensored interviews, news, commentaries and analyses that are unlikely to see daylight in Ethiopia.

Fortunately, here is where you find **TILA**, the un-disputably best source of information serving the Ethiopian Diaspora community in Europe & America with a proven record of excellence in journalism.

TILA is a political magazine published and distributed by patriotic Ethiopians around Hessen region in Germany. Tila appears in Amharic, English and Germany Languages every 3 months. It is a magazine of quality, responsibility and standard. Entertainment and sport are among our coverage issues next to Ethiopian politics.

As a reader, you are to get useful political and current news in **TILA** than any other publication can offer you. More comprehensive analysis and interpretations than any other media can present to you. In fact, these are some of the qualities of **TILA** that has made it the largest circulating magazine in its category. **TILA** magazine has also partnered with ethiomedia.com, ethiogermany.de, ethiopiazare.com and afroaddis.wordpress.com among others, to deliver reliable and high quality content to our visitors.

Don't take the chance of missing this spectacular political magazine. Subscribe to it today! We promise, you won't regret your decision. Reach us on tilamagazine@yahoo.de & tilamagazine.yolasite.com

## Tila Magazine is yours Magazine!


## ውድ አንባብያን

ጥላ መፅሄት በየሶስት ወሩ የምትታተም የፖለቲካ መፅሄት ናት።መፅሄቷ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሰረት አድርጋ በጀርመን አገር የምትታተም ቢሆንም መረጃ መረቦችን በመጠቀም መላውን ዓለም የማዳረስ ዓላማን አንግባ እየተንቀሳቀሰች ነው።

የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታና ጠቃሚ መረጃዎችን በማካተት ዝናን ያተረፈችው የጥምረት መፅሄት አዘጋጆች ያቋቋሟት ጥላ መፅሄት የስሟ ስያሜ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተበታተነ ሁኔታ የሚያካሂዱትን የትግል ሂደት በማስቀረት በአንድ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ ለማሳሰብና አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

የፖለቲካ ሃይሎች በተበታተነ ትግላቸው ጋት እንኳን መራመድ እንደማይችሉ በመገንዘብ የጋራ ትግል እንዲያካሂዱ ለማበረታታትም ጭምር ነው እ.ኤ.አ ከጥር 2012 ጀምሮ በዚህ ስም መፅሄቷ እንድትጠራ የወሰንነው።በመፅሄቷ አዝናኝና አስተማሪ ዝግጅቶች የሚካተቱበት ሲሆን ስፖርትም ትኩረት ያገኛል። ጥላ መፅሄት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን ያለምንም ገደብ በነፃነት የሚያቀርብበት ክፍት መድረክ በመሆኑ በመፅሄቱ የሚወጡት ፅሁፎች በሙሉ የፀሃፊዎቹን እንጂ የጥላ መፅሄት ዝግጅት ክፍልን የማይመለከቱ መሆናቸውንም መግለፅ እንወዳለን።

**ጥላ መፅሄት የእናንተው መጽሔት ናት !**



# EDITORIAL



# Ethiopia: Governmental ignorance

We have often criticized the ruling regime in Ethiopia for its willful ignorance of its own Constitution and rules, willful indifference and oversight of its duties under the supreme law of the land and flagrant disregard of its obligations under international law.


According to Ethiopian Constitution article 18, which is exactly copied from UDHR article 4&5 ``´ everyone has the right to protection against cruel, inhuman or degrading treatment or punishment. No one shall be held in slavery or servitude: but the reverse is happening on Ethiopians who are living in Saudi Arabia. The Saudi government and some arrogant Arabs made an amazing massacre against Ethiopians, who their ancestors gave the Saudi Muslims (followers of Prophet Mohammed) a shelter and everything to hide from their enemies.

Ethiopians have been living in Saudi Arabia for more than 50 years as law abiding citizens without any problem until recently. And there is no possibility for them to have become criminals in few weeks. But the problem relays on the Ethiopian government, the government is always ready for the counter attack than to be a frontline leader. Some of higher officials are still hiding behind bars not to talk to their fellow citizens (citizens who are in danger). The closing of the Jeddah Ethiopian consulate is also questionable.

The other amazing activity which was done by the government is harassing the peaceful protesters in Addis Ababa against the inhuman treatment of Saudi regime on Ethiopians. The government communication state minister said that the protesters had not got permission from the appropriate office. It is also against the country`s constitution of article 30 (the right of assembly, demonstration and petition). The protesters have no political intention at that time. We have got a national issue, and then we should have to act nationally.

So, you guys from EPRDF should have to differentiate national and party issues first before making a double Jeopardy. Are you the leaders of our people or the puppet of rich and stupid regimes like Saudi Arabia? We know now that you are the second one. There is a very good proverb in Germany language, which says ``Der Bulle vergasst, dass er ein Kuh war``. That means, the Bull forgotten that he was a cow.

It will not make a dent but it will deter the Saudi's how God is reacting swiftly and flooded the crime city after the atrocity and crime was glamorized. It is hard to say "that is it!" when people die but at this time we just want to say thank you for GOD for taking a vengeance for us. As always Tila wish you a nice reading. **Tila magazine is yours Magazine!**



# ርዕሰ አንቀጽ



# ኢትዮጵያ፡- መንግስታዊ አላዋቂነት

በኢትዮጵያ ያለውን ገዢ ስርዓት ሌላው ቢቀር ራሱ ባወጣው ህገመንግስት ለሰፈሩት የህግ የበላይነትና በስራቸው ለሚገኙት መርሆች ባለመገዛቱ እንዲሁም በዓለምአቀፍ ህጎች የሰፈሩትን መመሪያዎችና አስገዳጅ ትዕዛዛት በፈቃደኝነቱ በመጣሱ በተደጋጋሚ ስንወቅሰው ቆይተናል።

ከዓለምአቀፉ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ሰነድ ላይ ሙሉ በሙሉ የተቀዳውና በኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 18 ላይ የሰፈረው “ሁሉም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢሰብዓዊ ከሆነና ሰብዓዊነት ከጎደለው አያያዝና ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው።ማንም በባርነትና ነፃነቱን ከሚገፉ ነገሮች መጠበቅ አለበት።”ይላል። ነገር ግን በሳኡዲ አረቢያ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰው የዚህ አለምአቀፍ ህግ ተፃራሪ ነው። የሳኡዲ መንግስትና ማሰብ የተሳናቸው የአገሪቱ ዜጎች ለነብዩ መሓመድ ተከታይ ለሆኑት ቅድመ አያቶቻቸው ጥገኝነት በመስጠት ከጠላቶቻቸው ያዳናቸውን የኢትዮጵያ ህዝብ ውለታ ክደው በኢትዮጵያውያን ላይ ግድያና የአካል ማጉደል አድርሰዋል።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያውያን ላለፉት 50 ዓመታት የሳኡዲ አረቢያን ህግና ስርዓት ተከትለው ያለምንም ችግር በመኖር ላይ ናቸው።ስለዚህ በምንም ተዓምር በጥቂት ሳምንታት ወደ ወንጀለኛነት የሚለወጡበት ሁኔታ አይኖርም።ችግሩ የሚወድቀው በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ነው።መንግስት ችግሩ ተከስቶ በተለይ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዓለምን ካጥለቀለቋት በሁዋላ ይሄ እንደዚህ ነው ያ እንደዛ ነው ብሎ መልሶ ለማጥቃት ከሚንቀሳቀስ እንደ መንግስት ግንባር ቀደም መሪ ነው መሆን ያለበት።ጥቂት ከፍተኛ ባለስልጣናትም ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ እስካሁን የት እንደተሸሸጉ ለማወቅ ከብዶናል።በጅዳ የሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንስላ መዘጋቱም አጠያያቂ ነው።


ሌላው አስገራሚው የኢትዮጵያ መንግስት ድርጊት ደግሞ በሳኡዲ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰውን ግፍ ለመቃወም በአዲስ አበባ ሰልፍ በወጡት ኢትዮጵያውያን ላይ በፌዴራል ፖሊሶች የደረሰባቸው ድብደባና እስር ነው።ድርጊቱን ተከትሎ ለሚዲያ መግለጫ የሰጡት የመንግስት ኮምዩኒኬሽን ሚኒስትር ዴኤታው እንዳሉት ሰልፈኞቹ ከሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት ፈቃድ አላገኙም።ይህም የአገሪቱን ህገ መንግስት አንቀጽ 30 “የመሰብሰብ ሰልፍ የማድረግና ፊርማ የማሰባሰብን መብት” የጣሰ ነው።በመጀመሪያ ሰልፍ ማሳወቅ እንጂ ፈቃድ መጠየቅን ህገ መንግስቱ በቅድመ ሁኔታነት አያስቀምጥም።ሰልፈኞቹ የፖለቲካ ጥያቄ አልነበራቸውም።ጉዳዩ ብሔራዊ ጉዳይ ነው።ሲሆን መንግስት በደገፋቸው ካልሆነ ግን መብታቸውን ሊነፍጋቸው አይገባም።ብሔራዊ ጉዳይ ሲነሳ ብሔራዊ ምላሽ እንጂ የተናጠል ምላሽ አይገባም።

ስለዚህ ከኢህአዴግ ጎራ ያላችሁ ሰዎች የፓርቲና የአገር ጉዳይን ለይታችሁ በማየት በሳኡዲ የደረሰብን ውርደት ሳያንስ ዳግም ቅጣት አትቅጡን።ለመሆኑ የህዝባችን መሪዎች ናችሁ? ወይስ እንደ ሳኡዲ አረቢያ ማሰብ የተሳናቸው ሃብታም አገሮች መንግስታት አሻንጉሊት ናችሁ?አሁን ግን አውቀናል ሁለተኛው መሆናችሁን።በጀርመንኛ አንድ አባባል አለ።”ኮርማ ድሮ ላም እንደነበረ ረስቷል”።

በእርግጥ ደስ ያሰኛል ብለን ጮቤ የሚያስረግጥ ባይሆንም እግዚአብሔር ሳኡዲዎች ካደረሱብን ግፍ ወዲያውኑ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ዋና ከተማዋ ሪያድን በጎርፍ አጥለቅልቆ ከፍተኛ የሰውና የንብረት ኪሳራ አድርሶባቸዋል።ሰው እየሞተ እንዲህ ነው ወይም እሰይ አንልም።ግን እግዚአብሔር ይመስገን በደላችን ተበቀለልን ከማለት አናፈገፍግም።እንደ ሁል ጊዜው ጥላ መጽሔት የተለያዩ ወቅታዊ መረጃዎችን ይዛላችሁ ቀርባለች መልካም ንባብ ይሁንላችሁ።

**ጥላ መፅሄት የእናንተው መጽሔት ናት!**

# ለብቻህም እንኳን ብትሆን ትክክለኛውን እንጂ አብዛኛውን አትከተል




## የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር



በዘመነ ኢህአዲግ

የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፀንቶ
ታየ ህዝባዊነት ዳር እስከዳር በርቶ
ለሰላም ለፍትህ ለህዝቦች ነፃነት
በእኩልነት በፍቅር ቆመናል ባንድነት
መሰረተ ፅኑ ሰብዕናን ያልሻርን
ህዝቦች ነን ለስራ በስራ የኖርን
ድንቅ የባህል መድረክ ያኩሪ ቅርስ ባለቤት
የተፈጥሮ ፀጋ የጀግና ህዝብ እናት
እንጠብቅሻለን አለብን አደራ
ኢትዮጵያችን ኑሪ እኛም ባንቺ እንኩራ።
******************************

በ1984 ዓ.ም
ግጥም፦ደረጀ መላኩ መንገሻ፤
ዜማ፦ ሰሎሞን ሉሉ ምትኩ



በዘመነ ደርግ

ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ -ኢትዮጵያ ቅደሚ
በኅብረተሰባዊነት - አብቢ ለምልሚ!
ቃል ኪዳን ገብተዋል - ጀግኖች ልጆችሽ
ወንዞች ተራሮችሽ - ድንግል መሬትሽ
ለኢትዮጵያ አንድነት - ለነፃነትሽ
መስዋዕት ሊሆኑ - ለክብር ለዝናሽ!
ተራመጂ ወደፊት - በጥበብ ጎዳና
ታጠቂ ለሥራ - ላገር ብልጽግና!
የጀግኖች እናት ነሽ - በልጆችሽ ኩሪ
ጠላቶችሽ ይጥፉ - ለዘላለም ኑሪ።
**************************

በ1968 ዓ.ም
ግጥም፦በአሰፋ ገብረማርያም
ዜማ፦አቶ ዳንኤል ዮሐንስ



በንጉሱ ዘመን

ኢትዮጵያ ሆይ ደስ ይበልሽ
በአምላክሽ ኃይል በንጉስሽ
ተባብረዋልና አርበኞችሽ
አይነካም ከቶ ነፃነትሽ
ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ
አትፈሪም ከጠላቶችሽ።
ድል አድራጊው ንጉሣችን
ይኑርልን ለክብራችን።
****************

በ1919 ዓ.ም
ግጥም፦በቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ
ዜማ፦ኬቨርክ ናልባልድያን

# ኢትዮጵያዊው የፈጠራ ባለቤት በጀርመን

ነብዩ ተፈሪ መኮንን ይባላል። በሐረር ከተማ ተወልዶ ያደገ የ36 ዓመት ወጣት ነው። በስደት ህይወቱን መምራት ከጀመረ በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል።በስደት ላይ በጀርመን አገር ሄሰን ግዛት ፍሎርስ ሃይም ከተማ በመኖር ላይ ይገኛል።

በአገር ቤት በመምህርነት ተቀጥሮ ሲሰራ የአገሩን ህዝብ በሚችለው አቅም ለመርዳት የተለያዩ ሙከራዎችን ሲያደርግ መቆየቱም ይታወቃል።

በስደት ሕይወቱ የተለያዩ ልምዶችን የቀሰመው ወጣቱ ነብዩ በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጣርቶ የትምህርት ድጋፍ መርጃ ሊሆን የሚችል <u>መደመርና ማባዛት ያለ አንድ አለኝ ስሌት ማስላት</u> የሚያስችል የፈጠራ ባለቤት ሆኖ እውቅናው ተሰጥቶታል።

ኢትዮጵያዊው የዚህ ግኝት ባለቤት ነብዩ የኣለም ህዝቦች በተለይም ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች በግኙቱ ይጠቀሙበት ዘንድ ግኙቱን በጥላ መጽሔት ለአንባብያን አቅርቦታል።

በቀጣይም በመቀነስና በማካፈል ወቅት የሚያጋጥሙንን የአንድ አለኝ ስልት ለማቃለል የሚያስችል ምርምር ላይ መሆኑንም ለማወቅ ችለናል።

የፈጠራውን ባለቤት በኢሜል ለማግኘት ከፈለጉ በሚከተለው አድራሻ መጠቀም ይችላሉ።

<u>nebyutmn@yahoo.de</u> ወይም Patent DE102011100272A1 - Method for performing mathematical <u>nebyutmn@yahoo.de</u> ወይም Patent DE102011100272A1 Method - for performing mathematical <u>www.google.com/patents/DE102011100272A1</u>

**( Method for performing mathematical process e.g. addition without leaving counting value, involves adding results of processes without leaving carry over value for each time DE 102011100272 A1 )**

**ዝርዝሩን ማግኘት ትችላላችሁ። እኛ እንግዲህ እነሆ በረከት ብለናል።እናንተ ደግሞ ትገለገሉበት ዘንድ ምኞታችን ነው።**

የምስራች መደመር እና ማባዛትን ያለ አንድ አለኝ በቀላሉ ማስላት.

ለምሳሌ. በመደመር ሥሌት ወቅት ውጤቱ ከ 10 በታች ከሆነ ከፊቱ ዜሮ መፃፍ

Mathematik (* und + ) ohne übrig zu rechnen.
wenn beim Addieren die Ergebnisse wenig als 10 sein.in den Ergebnisse vorn Null zu schreiben .

Ich freue mich
dass ,ich diese Erefindung gefunden habe
die ganze Welt lachten aus Freude
Mathematik zu rechnen ohne übrig.

ደስተኛ ነኝ
አስደሳች ግኝት ሳገኝ
የዓለም ምሁር ሲረዳልኝ
በማስላት ያለ አንድ አለኝ::

Z:B
Meine Erfindung ohne übrig Rechnung wie leicht ist:!

```
1)        + 96
          +98
         ______      ( oder )
6+ 8:---- + .14    + 014
 9+9 ----   18 .     180
          ______    ______
            194      1 9 4
          ======    ====

2)        + 2148
          + 3219
           =====
8+9---     . .17   + 0017
4+1---     . 05 .    0050
1+2 --     03 . .    0300
2+3--     05 . . .   5000
          _______   ______
           5 3 67    5367
          =======   ======

1)         964
            *6
          ________      ( oder )
6*4---   +  . . 24       0024
6*6---      . 36 .       0360
6*9---      5 4 . .      5400
          ________      ______
            5784         5784
          =======       ======
```

```
2)             184
                *64
               ====       ( oder)
4*4--   +   . . 16      +  0016
4*8--       . 32 .         0320
4*1--       . 4 . .        0400
 .......
          _________      ________
            . 736           0736
          ========       =======

         +   .736    +    0736
6*4--        .24 .        0240
6*8--        48 . .       4800
6*1--        6 . . .      6000
          __________     _______
            11776         11776
          =========      ======
```

28.04.11
TMN
ተመን

# ስደት እስከመቼ?

**Tadesse Bezabih /Berlin**

ሰው ተወልዶ ባደገበት አግብቶ በወለደበት ማህበራዊ እሴቱን በጠበቀበት በወንዙና በምድሩ በሰላምና በደስታ መኖሩን እንደማይጠላ የሚታመን ሐቅ ነው።ይህ ሊሆንና ሊረጋገጥ የሚችለው ማንኛውም ሰው መሰረታዊ የሆኑትን ግልና የጋራ መሻቶቹ ዴሞክራሲያዊ በሆኑ መንገዶች ሲረጋገጡለት ብቻ ነው።እነዚህ ነገሮች ተረጋገጠ ማለት ማንኛውም ሰው በነፃ መናገር መሰባሰብ በነፃ ሃሳቡን የመግለጽ የመምረጥ የመመረጥ የሚጠበቅበትን ለማበርከት ወዘተ..እንዲችል ያደርገዋል።

ነገር ግን የአንድ መንግስት ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በጨካኝና ዴሞክራቲክ ባልሆኑ መሪዎች አማካኝነት አንድን ህዝብ /ብሔር መሪ ሌላውን ህዝብ ደግሞ ተመሪ ከማድረጉም ባሻገር ለአገሩ ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ እንዲኖር አድርጎታል።በዚህም ምክንያት ሁል ጊዜ በሰቆቃና በፍርሃት ከመኖሩም በላይ ለከፋ የሰቀቀን ኑሮ ለመከራና ስቃይ ወዶ ሳይሆን በግዱ እንዲዳረግ ያደርገዋል።

እነዚህ ከፍተኛ ተፅዕኖዎች ማንኛውም ሰው ለአገሩና ለህዝቡ የሚጠበቅበትን እንዳያበረክትና እንዳይወጣ ከማድረጉም ባሻገር የሚደርስበትን መከራ ለመሸሽ ስደትን እንደ አማራጭ ተጠቅሞበታል።ግን እስከ መቼ ስደት?

ማንም ሊረዳውና ሊገነዘበው በማይችለው መንገድ ራሱን እስከ መስዋዕት ታላቅ ዋጋ በመክፈል ላይ ይገኛል።እረ ለመሆኑ ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ መብቱ ቢከበርለት እንደፈለገ ሰርቶ ቢያድር እናውቅልሃለን ሳይሆን እኔ ለራሴ አውቃለሁ ብሎ ቢወስን ወዘተ...ለምን መሰደድ ያስፈልገዋል?

ስለዚህ መልካም አስተዳደርና የህዝብ ተጠቃሚነትን እንዲሁም ዴሞክራሲን ለማምጣትና አምባገነኑን መንግስት ለማስወገድ እንታገል።

# መሄጃ ያጣ ትውልድ

**Sara Mesfin/Gießen**

ግን ምን አድርገን፣ ምን ሰርተን፣ ምንስ አስቀይመን ይሆን እንዲህ ከሰው የተለየ መከራ የሚደርስብን? እኔ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ ያነበብኩት የአይሁዳውያን ግፍ ጌታ ላይ ያደረሱት መከራ በራሳቸው አንደበት "ደሙ በልጅ ልጆቻችን ላይ ይሁን" ብለው ስላሉ ያ የንፁህ ክርስቶስ ደም ለአንድ ሺ አመት በላይ በአለም ተበትነው እንዲቀጠቀጡ እና በግፍ እንዲሞቱ መደረጉን አውቃለሁ።

ከሀምሳ እና ስልሳ አመት በፊት የናዚወችን በአይሁዳውያን ላይ የተደረገ ጭፍጨፋ አይነተኛ ምስክር ነው። እነሱ በሀጢያታቸው የመጣ መከራ ነው እንበል እኛስ ምን አድርገን ነው ይህ ሁሉ ግፍ በሀገራችን፣ በሰው ሀገር እንደሰው ሳንቆጠር የምንሰቃየው? በሀገራችን በዘረኛው የወያኔ መንግስት ግፍ እንደሁለተኛ ዜጋ ተቆጥረን ፣ ስንናገር እና ስንቃወም እየታሰርን፣ እየተደበደብን፣ እየተገደልን፣ በውጭ ሀገር ከሰው በታች እንደ እንስሳ ተንቀን በሰው ላይ የማይደርስ መከራ እየደረሰብን፣ ግን እስከመቸ ወዴት እንሂድ???

ያ የአያቶቻችን አልነኬ ባይነት ፣ ያ የአፍሪካ የነፃነት ተምሳሌትነት ፣ ያ የሀይማኖት ሀገርና ኩሩ ህዝብ ዛሬ ምን ነካው ? ዛሬ የት ሄደ? እድሜ ለወያኔ። መሬታችን እና ህዝባችን ለአረብ እየሸጠ ያዋረደን፣ ያስደፈረን ቀንደኛ ጠላታችን ወያኔ ነው። መንግስት እንደሌለን፣ ሀገር እንደሌለን በማንም ጋጠወጥና ጨካኝ አረብ መጫወቻ ሁነን ደማችን ደመ ከልብ ሆኖ እንዲቀር ያደረገን ወያኔ ነው።

ሀገር ቤት ችግር፣ ርሀብ፣ ነፃነት እና ተስፋ ማጣት፣ እህቶቻችን ወግ ማረጋቸውን ሳያዩ፣ ለመማር ሳይችሉ፣ ወንድሞቻችን ተምረው ስራ ቢያጡ፣ የሱስ ተጠቂ እና የቤተሰብ ተጧሪ ቢሆኑ፤ ራሳችን ለማቆም ስንውተረተርም ይህን ደግፊህል፣ እኔን ተቃውመሀል፣ ለእኔ አባል አልሆንክም እያለ መግቢያ መውጫ ሲያሳጣን ሞትን ቢሆን ተጋፍጦ በበርሀ፣ በጨለማ፣ ሞት ባለበት ጀልባ፣ እንዲያልቅ እየሆነ ነው። እስራቱ፣ ግርፋቱ፣ ዱላው፣ አስገድዶ መደፈሩ፣ ውስጥ አካሉን ማጣቱ ስንቱን እንቁጠረው ይህን ሁሉ ደርሶበት ሰው ሀገር ሲገባ እንደሰው ሰርቶ መኖር አልችል ብሎ በአረመኔ አረቦች ከተሰቃየ በኋላ የሞት ቀኑን የሚቆጥረው ወገናችን ስንቱ ነው።

አገራችን ላይ በተስፋ፣ በነፃነት፣ በዲሞክራሲ፣ በእድገት እንድንኖር በአንድነት ተነስተን ወያኔን ልናጠፋ ግድ ይለናል። ወያኔን እና ባንዳወቹን እስካልቀበርን ድረስ የሀገራችን መከራ የህዝባችን ችግር ይብሳል እንጂ አይቆምም። ለህዝቡ ለሀገሩ ምንም ግድ የሌላው ሌባ መንግስት የግድ መጥፋት የግድ መደምሰስ አለበት። ያገሬ ህዝብ

ወይ ይህ የሚሆነው በተባበረ ክንድ ስንነሳ ነው። በተለይ ሀገር ቤት ያለው ወጣት በድፍረት ወያኔ ላይ ሊነሳ ግድ ነው። ዋናው የትግል ቦታ እዚያው ሀገራችን ውስጥ ነው። ይህን አድርገን ሀገራችንን ዳግም የነፃነት ተምሳሌት የምትሆንበት ቀን ቅርብ እንዲሆን ፈጣሪ ይርዳን።

# ትልቅ የመከራ ተራራ

**Ybekal Engeda Tsegaye/ Kassel**

የሰው ልጅ ከተወለደበት አገር እንኳን ለመሰደድ ለአንድ ቀን ለመሄድ አይፈልግም።በተለይም የተፈጥሮ ህግጋት የኑሮ ቦታ ለውጥና እራሱን ለማዝናናት ወይም ቤተሰቡን ጓደኛውን ለመጠየቅ ካልፈለገ በስተቀር ከሃገሩ ተለይቶ ለመኖር እንደማይፈልግ እሙን ነው።

አለመታደል ሆነና አገራችን በህዝቧ ላይ በተለይም በዚህ ትውልድ ላይ ትልቅ የመከራ ተራራ ወድቆበታል።ዛሬ በህወሓት ኢህአዴግ መንግስት የፖለቲካና የማህበራዊ ኑሮ ምስቅልቅልነት የተነሳ በርካታ ዜጎች በየበረሃው ለሞት ለአካል መጉደልና እስር እየታደረጉ ናቸው።በስደት ላይ።ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ከሰሞኑ በሳኡዲ አረቢያ የፀጥታ ሃይሎችና ነውረኛ አረቦች በዜጎቻችን ላይ የተወሰደው ኢሰብአዊ ድርጊት ነው።ዜጎቹን ያልታደገው የኢህአዴግ ስርዓትም ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ራሱ ነው።

አሁን በተጨባጭ እንደምንመለከተው ከሆነ አገራችን ፍፁም ኢፍትሃዊ በሆነ አምባገነን አስተዳደር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ወድቃለች።ምክንያቱም ገዢው ፓርቲ ላለፉት 22 ዓመታት ስልጣኑን ኢዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተቆጣጥሮት ይገኛልና። በሰለጠነው ዓለም በስልጣን ላይ የመቆያ እድሜ ቢበዛ 8 ዓመታት ነው።

ታዲያ ወገኖቼ ምንድነው የምንጠብቀው? ከዚህስ የከፋ ምንስ ነገር አለ?ለቀጣዩስ ትውልድ የምናስተላልፈው ምንድን ነው?ድህነትን ስደትን መሰደብን ንቀትን ሁሉን በቃ ማለት ይጠበቅብናል።እኛ መስዋዕት ሆነን የቀጣዩን ትውልድ ሰቆቃ ልንከላከል ይገባል።

አንድነት ሃይል ነው ውስጣችን ያለውን ሃይልና የታመቀ ብሶት በመጠቀም ለእናት አገራችን መቆም ይጠበቅብናል።አገራችን ውበታችን መታወቂያችን ናትና ልንጠብቃት ይገባል።የወያኔን አገዛዝ ከመቼውም ጊዜ በላይ በመታገል ማስወገድ ግድ ይለናል!ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።አሜን

# በሳኡዲ አረቢያ ለደረሰው ግፍ ተጠያቂው ማነው?

**Michael Feysa/Amberg**

በቅርቡ በሳኡዲ አረቢያ ባሉ ኢትዮጵያውያን ላይ ለደረሰው ግፍና ኢሰብዓዊ ከአገር ማባረር ችግር ተጠያቂው የሳኡዲ መንግስት ብቻ ነው ብዬ አላምንም።ኢትዮጵያን የሚያስተዳድረው የወያኔ መንግስትም የራሱ ድርሻ አለበት። ድርጊቱም የመንግስት ተብዬውን የህዝብ አስተዳደር ችግር ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነውና።

መልካም የሚባሉ አረቦች እንዳሉ ሁሉ ማሰብ የተሳናቸው ከጥላቻው ራቅ አድርገው መመልከት የማይችሉ ነውረኞችም እንዳሉ መዘንጋት የለበትም።እንኳንስ የአገሪቱ መንግስት "ህገወጥ" ያላቸውን ይቅርና አረቦቹ በዜጎቻችን ላይ በጠራራ ፀሃይ የሚፈፅሙትን ግፍ ለሚያውቅ መንግስት ነገሩ ከመፋፋሙ በፊት ዜጎቹን አሳምኖም ቢሆን ማስወጣት ነበረበት።እምቢ ያሉም ቢኖሩ ጉዳዩን በቤተሰቦቻቸው በጓደኞቻቸው በማህበራዊ ድረ-ገፆችና በሚዲያ ሳይቀር ችግሩንና የሳኡዲ መንግስትን ርህራሄ የጎደለው ውሳኔ ማወጅና መላ ሊበጅለት ይገባ ነበር።

ሁል ጊዜ መንግስት እንዴት ጭራ ይሆናል።ክራይስስ ሲያጋጥምም የክራይስስ ማኔጅመንት ክህሎትን በማዳበር አገርን ከውርደትና ከማስደፈር መጠበቅ ይገባል።ካልተቻለ ደግሞ ለሚችሉት ስራውን ቦታውን ማስረከብም ብልህነት ነውና ለደረሰው ችግር የወያኔ ኢህአዴግን ህዝባዊነት ጥያቄ ውስጥ የከተተ በመሆኑ ለችግሩ ከሳኡዲ መንግስት ባልተናነሰ ወይም በላይ ተጠያቂው ራሱ ብቻ ነው።ከስደት የተላቀቀች አገር እስክናይ ህብረታችንን እናጎልብት!ሰላም

# እንግልትና ስቃይ በዛ

**Helen Tesfay Kebede/Gießen**

ዛሬ በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች የሚነሱ የዴሞክራሲ ጥያቄን ለማፈን የሚደረገው አፈናና ግድያ ተጧጡፏል።ለዚህም መሸፈኛ እንዲሆነው አሸባሪዎች ፀረ-ህዝብ የሚል ስያሜ በመለጠፍ የአለምን ህዝብ እያጭበረበረ ያለ አደገኛ ማፍያ መንግስት የህዝቡን ተስፋ በማጨለም ጥቂቶች የሚዝናኑበት ብዙሃኑ አንገቱን የሚደፋበት ጭንቀቱ ስደቱ ስለበዛበት እትብቱ የተቀበረበትን ሃገሩን በመተው በባህር በበረሃ በውሃ ጥም በረሃብ አልፎም በህገ ወጥ አስኮብላዮች ህይወቱን እያጣ ነው።

የኑሮ ውድነት የጤና ችግር የትምህርት ጥራት መጓደል ስራ አጥነት የዴሞክራሲ እጦት የመልካም አስተዳደር ችግር ለኢትዮጵያውያን በጉልበት የተጫነባቸው የወያኔ ገፀ በረከቶች ናቸው።

ህዝባችን የመከራና የስደት ጊዜው ቆሞ በፖለቲካ በኢኮኖሚ በማህበራዊ መስኩ ዓለም የደረሰበት ደርሶ የሰለጠነና የተማረ የሰው ሃይል ማፍራት ነው የምንሻው እንጂ በጎሳ ተከፋፍሎና ሃገር ተከፋፍላ ትውልዱ በጥርጣሬ አይን እየተያየ አንድነቱ ተሸርሽሮ አቅሙ ደክሞ ማየት ትልቅ ውርደት ነው።

የተበደለ የተጨቆነ መብቱን የተነጠቀ ህዝባችንን ነፃ ለማውጣት በሃገር ውስጥ ይሁን በውጭ አገር ያለን ኢትዮጵያውያን በዕውቀታችን በጉልበታችን በገንዘባችን ትግሉን በመደገፍ በአንድነት በመቆም ወያኔን ማሽመድመድ የምንችልበት ወቅቱ አሁን ነው።ስለሆነም አምባገነኑን ስርዓት በጋራ ክንዳችን በቃ ልንለው ልናስወግደው ይገባል።

# ባርነት እስከ የት?

**Tigist Belay Demissie/ Pfarrkirchen**

በአገራችን ኢትዮጵያ እኩልነት ወንድማማችነት ያሳጣው አምባገነኑ የወያኔ መንግስት ስልጣን በፍቃዱ ሊያስረክብ ባለመቻሉና ባለመውደዱ የተነሳ ዴሞክራሲን በስጦታ መልክ ከሱ የሚጠብቅ ግለሰብ አይኖርም።የወያኔ መንግስት ላለፉት 22 ዓመታት አገራችንን በግድ ሲያስተዳድር የህዝባችንን ነፃነት ከመንፈግ አንስቶ ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ ፈጥሯል።

በዚህም መሰረት ኢፍትሃዊ የሆነውን ስርዓት ታግለን መጣል አለብን።ይህንን ህዝቦችን ከህዝቦች የሚከፋፍል አምባገነን ስርዓት ለሰላም መናጋት ለዜጎች ስደት የዳረገንን ስርዓት ማስወገድ የሁላችንም ሃላፊነት ነው።

ሰላም የሁሉ ነገር መሰረት እንደመሆኑ ሁሉ ነፃነት ማለት ከተገዢነትና ከባርነት ተላቆ በራስ ማሰብን ይጠይቃል።ሆኖም በወያኔ መንግስት ይህ ተነፍጎን ስለቆየን አሁን በቃህ ልንል ይገባል። የባርነት ገደቡ የት ድረስ ነው? በራስህ ሰው ለባርነት መዳረግ ደግሞ የሞት ሞት በመሆኑ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን እጅ ለእጅ ተያይዘን ነፃነታችንን ማረጋገጥ ግድ ይለናል!

# ሀገራችንን ከስቃይ እንታደጋት!

**Meseaily Dedejnie/ Alsfeld**

ወልዶ ያሳደገውን እናት መካድ ማለት ጡት መካድ ማለት ነው።ይህን ለማለት ያስደፈረኝ በአገር ውስጥ የሚደረጉ ጭቆናዎችን የወያኔ ገዢ ፓርቲ እንደሚፈፅመው ሁሉም ዜጋ ስለሚረዳ በጋራ የሚስማማበትም አባባል በመሆኑ ነው። በስርዓቱ እየደረሱብን ባሉት ኢፍትሃዊ አሰራሮች ህዝባችን ለረሃብ ለኢኮኖሚ ድቀትና ለፖለቲካ አረንቋ ተዳርጓል።ይሄን ደግሞ እንኳንስ እኛ ነዋሪዎቹ የውጭ ዜጎቹም የሚያረጋግጡት ነው።

ሆኖም ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያልሰፈነባት አገር ከፍተኛ ፈተና ውስጥ እየተዘፈቀች በመሆኑ የሁላችንም አንድነት ያስፈልጋል።ስርዓቱን ለማስወገድ።ለምን ቢባል ባገዛዙ ለስቃይና ለመከራ የተዳረግነው እኛው ነንና መፍትሄውም ያለው በእኛው ስለሆነ።

በመሆኑም የአገራችን ጋዜጠኞች ፖለቲከኞች እንዲሁም በዘርና በጎሳ መድሎ ለእስር የተዳረጉ ውድ የአገራችን ዜጎችን ካሉበት ማህበራዊ ቀውስ ለማውጣት በዋነኛነት ደግሞ ህዝባችንን ከአምባገነኑ ስርዓት በተባበረ ክንዳችን ከጫንቃው ለማላቀቅ በጋራ በቃህ ልንለው ይገባል።

**We are the voice of the voiceless !**
**Tila Magazine**

# ህልመኞቹ እነ ሀይለማርያም ደሳለኝ ወይስ ግንቦት ሰባት?

**Girum Kelemu and Netsanet Mamo/Gießen**

አቶ ሀይለማርያም ደሳለኝ በፓርላማ ስለ ግንቦት ሰባት ሲጠየቁ ህልመኞች ናቸው፤ ከህልማቸው ሲነቁ ያውቁታል ምናምን የሚል እንጨት እንጨት የሚል ቀልድ አይሉት ቁም ነገር ተናግረው ነበር። ታዲያ አሁን የግንቦት ሰባት ስራ እንቅልፍ አሳጥቶዋቸው በውን በህልማቸው እያቃዣቸው እንዳለ ሰሞኑን ባደረጉት የመግደል ሙከራ በደንብ አሳዩን።

ግንቦት ሰባት ህልመኞች ሳይሆኑ እውነተኞች እንደሆኑ በሰሞኑ የመግደል ሙከራቸው ራሳቸው አረጋገጡልን። በየጊዜው በትልልቅ ሚዲያወች ሳይቀር ውሸትን እና አይኔን ግንባር ያድርገው አይነት የድርቅና ወሬን የሚናገሩት አቶ ሀይለማርያም እኛ ከህልም ቅዥት ያለፈ አክብደን አናየውም አሉ ፣ እውነቱ ግን ሌላ ነበር። ባንድ በኩል ግን ወያኔ እና አቶ ሀይለማርያም የተለያዩ ስለሆኑ ለእሳቸው የሚነገራቸው ህልም ነው ፣ ግንቦት ሰባት ምንም አያመጣም፣ ስለዚህ እንዲህ ብለህ ተናገር ተብለው ሊሆን ይችላል። እውነቱ ግን ግንቦት ሰባት ህዝባዊ ሀይል የወያኔ ራስ ምታት እና ጭንቀት ከሆነ ሰነባብትዋል። እናም ወያኔ ይህን ህዝባዊ ሀይል ለማጥፋት ከላይ ታች እያለ እንደሆነ በተግባር የሰሞኑ ስራቸው አሳይቶናል።

እዚህ ላይ ግን በጣም የገረመኝ ነገር የኛን ሀገር የስለላ ስራ ነው። በእውነቱ በጣም ያሳፍራል። በ21ኛው ክፍለ ዘመን እንዲህ የሞተ እና ተራ የስለላ ስራ እንዲያውም በመንግስት ደረጃ መስማት በጣም ያሳዝናል። እኛ ወያኔ እንደሚለው አሸባሪ ጠላት ቢኖርብን ያለአንዳች ማስጠንቀቂያ ህዝባችን በየቀኑ ያልቅ ነበር። እንኳን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና በረቀቀ የማሸበር ተግባር የተሰማሩትን ትልልቅ አሸባሪወች ይቅር እና ተራ ሌባ እንኳ ወያኔ እንደማይዝ አረጋግጦልናል። ወያኔ ሁሉም ቦታ የሱን ጀሌወች ብቻ ሰብስቦ ሀገሪትዋን ወደ ጨለማ ቀየራ። ብቃት የሌለው መሪ፣ ብቃት የሌለው ፖለቲከኛ፣ ብቃት የሌለው አስተዳደር፣ብቃት የሌለው የትምህርት ስርአት፣ ብቃት የሌለው የስለላ እና የደህንነት ስራ ሀገሬን ደንቁረው አደነቆሩሽ። ህዝባችን እውቀት እና መሪ በማጣት ጠፋ። ወያኔወች ያላቸው አንድ እና አንድ ነገር ነው ንፁህንን ማፈን፣ ማሰቃየት አፀያፊ ነገር መፈፀም፣ ማሰር እና መግደል።

በዚህም ሆነ በዚያ ወያኔወች በቀላሉ የሚፈረካከሱ ውስጠ ባዶ መሆናቸው ከቀን ወደ ቀን ስራቸውን እያየን ነው። ግንቦት ሰባትም ሆነ ሌላው የዲሞክራሲ ሀይል በህብረት ጠንክሮ ከሰራ፣ ህዝባችን ያለመከፋፈል በአንድነት ከቆመና ወያኔ ላይ ከተነሳ በአረብ ሀገራት ከአየናቸው አመፆች በጣም ባነሰ ጊዜ ውስጥ ወያኔ ይወድማል። የወያኔ ጥንካሬ ሳይሆን የኛ ሀሞት እና ወኔ፣ ቁጣ እና ጭካኔ ማጣት ነው ለነሱ የልብ ልብ የሆናቸው። እጅ ለጅ ተያይዘን የሚደርስብንን መከራ ማስቆም አለብን ። በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ እኛ መከራ ላይ ነን የትም ብንሄድ ሀገራችን ነፃ እስካልወጣች ድረስ የኛ መከራ ቀጣይ ነው።

ሀገራችን ላይ በተስፋ፣ በነፃነት፣ በዲሞክራሲ፣ በእድገት እንድንኖር፣ በአንድነት ተነስተን ወያኔን ልናጣፋ ግድ ይለናል። ወያኔንና ባንዳወቹን እስካልቀበርን ድረስ የሀገራችን መከራ የህዝባችን ችግር ይብሳል እንጂ አይቆምም። ለህዝቡ ለሀገሩ ምንም ግድ የሌላው ሌባ መንግስት የግድ መጥፋት የግድ መደምሰስ አለበት። ይህ የሚሆነው በተባበረ ክንድ ስንነሳ ነው እና በተለይ ሀገር ቤት ያለው ወጣት በድፍረት ወያኔ ላይ ሊነሳ ግድ ነው ። ዋናው የትግል ቦታ እዚያው ሀገራችን ውስጥ ነው። ይህን አድርገን ሀገራችንን ዳግም የነፃነት ተምሳሌት የምትሆንበት ቀን ቅርብ እንዲሆን ፈጣሪ ይርዳን።

## <u>የስደት ውርደት በዛ</u>!

# ኢትዮጵያዊነትም ረከሰ...

Belay Fikre/Gießen

በሳዑዲ ዓረቢያ በኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ላይ እየተፈጸመ ያለውና እየተስተጋባ ያለው አሰቃቂ ግድያና ድብደባ ይዘገንናል፣ ይሰቀጥጣል፣ ያቅለሸልሻል፣ አረመኔያዊ ነው። የሳዑዲ ዓረቢያ መንግሥት የራሱን ሕግ ማስከበር እንዳለበት እናምናለን። በሕገወጥ መንገድ አገሪቱ ውስጥ የገቡትን ሰዎች ወደ አገራቸው ቢመልስ ወይም ቢያባርር ተቃውሞ የለንም። ጥያቄዎችንና ተቃውሟችን ግን በሕገወጥ መንገድ የገቡትን ኢትዮጵያውያን ለምን መለስካቸው? ለምን አባረርካቸው? የሚል አይደለም። ሕገወጦችን መቆጣጠርና ሕግን ማስከበር የማንም አገር መብትና ኃላፊነት ነውና። ነገር ግን በሕገወጥ መንገድ የገቡትን ኢትዮጵያውያን በሕጋዊ መንገድ ወደ አገራቸው ይመልሳል ወይም ይቀጣል እንጂ፣ ግድያና ማሰቃየት ማካሄድ የለበትም፣ አልነበረበትም።

እኛም እንደምንከታተለው የዓለም መገናኛ ብዙኃንም እያስተጋቡት እንዳለው፣ በመጀመሪያ ከኢትዮጵያ የሄዱት የቤት ሠራተኞች እንደ ባርያ እንጂ እንደ ነፃ ሰው አይታዩም፤ እንደ እንስሳና እንደ ባርያ ነው የሚቆጠሩት፣ በሕጋዊ መንገድ የገቡትም ጭምር። ከዚያም አልፎ በየቤቱ ፖሊስ እየገባ ሕገወጥ ናችሁ እያለ ሲገድልና አስከሬን በየጎዳናው ሲወረውር በግልጽ በሚሰቀጥጥ ሁኔታ እየታየ ነው።

የሳዑዲ መንግሥት የራሱን ሕግ የማስከበር መብት እንዳለው ሁሉ፣ ማክበር ያለበትና የሚገደድባቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕጎች እንዳሉም ሊገነዘብና ሊተገብር ይገባዋል። በተለይም በዘፈቀደ አንዳንድ የሳዑዲ ዓረቢያ ተወላጆች የሚፈጽሙት ግፍ አልበቃ ብሎ፣ የመንግሥት የፀጥታና የፖሊስ ኃይል ቤት ለቤት እየገባ ግፍና ወንጀል በኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ ሲፈጽም፣ በማያወላዳ መንገድ ዓለም አቀፍ ሕግን መጣስ ነው።ሕግ መጣሱና ወንጀል መፈጸሙ አሳዛኝ መሆኑ

እንዳለ ሆኖ፣ በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያውያን በባህልና በታሪክ የማይገናኟቸው አውሮፓና አሜሪካ ሄደው እንዲህ ዓይነት ግፍ አልተፈጸመባቸውም። ለዘመናት በታሪክ፣ በባህል፣ በቋንቋና በሥነ ልቦና ከሚቀራረቡት የሳዑዲ ዓረቢያ ሕዝብ ይህ ዓይነቱ ግፍ ሲደርስባቸው የሚፈጥረው ስሜት ውግዘት ብቻ ሳይሆን ምፀትም ነው።

ሕዝባችን ከሳዑዲ ዓረቢያ ሰዎች ጋር ብቻ ሳይሆኑ ከሌላው ዓለም ሕዝብ ጋር በአገሩም ሆነ በውጭ በፍቅርና በመተሳሰብ መኖር የሚችል ነው። በሳዑዲ ዓረቢያ እየተፈጠረ ባለው አስደንጋጭ ድርጊት እንደ ኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ብዙ ልንማረውና ልንፈጽመው የሚገባን ነገር አለ።

ከሁሉም በፊት እንደ መንግሥትም እንደ ሕዝብም ይህንን ድርጊት በይፋና በግልጽ ልናወግዘው ይገባል። አላስፈላጊ ረብሻና ግርግር በመፍጠር ሳይሆን ድርጊቱን በትክክል እንዳወቅነው፣ ሕገወጥና አረመኔያዊ እንደሆነና በጥብቅ እንደምናወግዘው በግልጽ መልዕክታችንን እናስተላልፍ።

ይህ ሁሉ ግፍ ብሄር፣ ሃይማኖት፣ ፆታ፣ እድሜ፣ ፖለቲካ ሳይለይ ኢትዮጵያዊነት ላይ የተወሰደ ርምጃ ነውና ሁሉም በያለበት ድምጹን ያሰማ። እምዬ ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር!!!

# ውሃን ለቅጣት መሳሪያነት!

**Tigist Alebachew/Bayreuth**

ውሃ ማግኘት በሳምንት አንድ ቀን ብርቅ እየሆነ መጥቷል።እንዲሁም አዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገነቡት ኮንዶሚኒየም ቤቶች በአሁኑ ሰዓት በውሃ እጥረት በመጥፎ ጠረን የሚበከሉ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ነዋሪዎች በአሁኑ ሰዓት በከተማው ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች የተለያዩ የህዝብ ሽንት ቤቶችና የሆቴሎች መፀዳጃ ቤቶች እያጣበቡ እንደሆነ ሲታወቅ እንዲሁም አንዳንዶቹ እድለኛ ከሆኑ ስራ ካላቸው ሁሉንም ነገር በመስሪያ ቤቶቻቸው አጠናቀው እንደሚወጡ ነው የሚነገረው።

አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና ናት።ነገር ግን በሁሉ አገር ዋና ከተማ ግን ውሃ የለም መብራት የለም ትራንስፖርት የለም መንገድ የለም።ይሄ ደግሞ ለገዢው ፓርቲ ትልቅ እፍረት ነው።በአፍሪካ መዲናይቱ አዲስ አበባ ህዝቡ ዉሃ የሚያገኘው ከዝናብ መሆኑ በሚነገርበት በዚህ ዘመን ገዢው ስርዓት በቁጥር አደግን የሚለን የት አለ?ይሄ ሃቅ እድገትን የሚያሳይ ይሆናል ወይ?።

ትልቁ ችግር ግን የመንግስቱ ያልተቀናጀ አሰራር ነው።መንገድ ለመስራት ውሃን ማበላሸት መብራት ለማስገባት ወሃን ማቋረጥ በአጠቃላይ እየከፋ የመጣው ችግር ደግሞ የፖለቲካ ተቃውሞ ወደሚበረክትባቸው አካባቢዎች ውሃን በቅጣት መሳሪያነት መጠቀም የከፋው ሆኗል።በውሃ እጥረት የሚሰቃዩት ነዋሪዎችም "አወይ ስልጣኔ" እያሉ ነው!

# ወዳልተፈለገ ስደት

**Tadele Brook Biru/Berlin**

ስደት በተለያየ መልክ ሊታይ ይችላል።እኔ ብዙውን ጊዜዬን በስደት ነው ያሳለፍኩት።ህይወቴ በስደት የተሞላ ነው።ብዙ ስል የተለያየ ሃገር ዞሬያለሁ ማለቴ አይደለም።በሃገሬ በኢትዮጵያ ሳለሁ አንድ ቦታ ረጅም ጊዜ ቆየሁ ከተባለ አንድ አመት ብቻ ነው።በብዙ ቦታዎች ኖሬአለሁ ምክንያቱም ወያኔ የሚያራምደው የጎሳ ፖለቲካ የመሬት ሽያጭና የፖለቲካ ችግሮች አንድ ቦታ ረግቼ እንዳልኖር አድርጎኛል።

አሁንም የመሬት ሽያጩና የህብረተሰቡ ንብረት ብዝበዛ በገበሬው በደሃው ህዝብና በነጋዴው ላይ ከፍተኛ የዘረፋ እንቅስቃሴ የወያኔ መንግስት እያከናወነ ይገኛል።ህይወት ማጥፋት የነበረውን መንገድ ተንተርሶ የሙስና ወንጀሎችን ማስፋፋትና በማንአለብኝነት ወገኖቻችን ላይ በደል ማድረሱ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ወዳልተፈለገ ስደት በመዳረግ ላይ ናቸው።

ታዲያ ወንድምና እህቶቼ ነገ ማነው ይህቺን አገር ከዘራፊው ከቀማኙ ከገዳዮና ከአምባገነኑ የወያኔ መንግስት የሚታደጋት? ጥያቄው የሁላችንም ነው።

# የወያኔ ጉዞ የእርስ በርስ መበላላት እየሆነ ነው!

**Tigist Kurabachew/ Nürnberg**

የወያኔ ገዢዎች እርስ በርሳቸው ሲበላሉ ሲጋደሉ ያየች አንዲት አዝማሪ ስታንጎራጉር "ጎጃሜ ቡዳ ነው ቡዳ ነው ስትሉ፣ አላያችሁም ወይ ወያኔዎች ሲባሉ" በማለት የወያኔን ሰው በላነት ትልቁን የታሪክ ጠባሳ እንዲህ በዜማ አንጎራጉራዋለች።እና ወያኔዎች ለእኛ ግራ የሚገባን ነገር የእናንተ እርስ በርስ መባላት ሳይበቃችሁ ምሲኪኑ ህዝብን ከጭንቅላቱ ጀምሮ እየበላችሁ አቅም ማሳጣት ልብ መስለብ የኢኮኖሚ እድገትን ያመጣል ወይ?የትስ ያደርሳችሁዋል?

ለምን ቢባል የዝንጀሮ መንገድ ቢከተሉት ገደል ነውና የእናንተ ታሪክ ዞሮ ዞሮ የእርስ በርስ መበላላት የመናቆር አልፎ ተርፎ ህዝብን መብላት ታሪክን ማጥፋት ነው።አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ነኝ የሚሉት ነገር ግን በህወሓት የበላይ ገዢነት እንደ ፔንዱለም እየተወዛወዙ ለሚገኙት አቶ ሃይለማርያም ከበፊቱ ሚኒስትር አመራር የወረሱትን ሰይጣናዊ አስተሳሰብና ፖሊሲዎች ካላስተካከሉ በምንም መልኩ አገሪቱ ልታድግና ሰላም እናደማይሰፍንባት ይገንዘቡ! ለነገሩ ይህን ያውቃሉ ሰይጣን እያወቀ አይደለም የሚያጠፋው እርስዎስ ከወንድሞ ከሰይጣን በምን ተሻሉ? እንዲያውም ባሱ እንጂ ስለዚህ

ያስቡበት እያልኩኝ የምትባሉም ከሆነ ከቡርነትዎ እርስ በርሳችሁ ተበላልታችሁ እለቁ።ቦታውን ግን ቀድማችሁ ለህዝብ አስረክቡ!ምክሬን ቢያደምጡኝም መልካም ነው።

# ድር ቢያብር አንበሳ ያስር!

**Roza Teshome/Würzburg**

በማንኛውም ፓርቲ ውስጥ አንድ ሰው ብቻውን ባዶ ነው ወይንም በሌላ አገላለፅ ኢምንት ነው ሃይል የለውም ስርዓት አይኖረውም አይበረታም።አላማዉ ግላዊ ነው ብቻውን የጤፍ ቅንጣት ነው።ጤፍ ብቻውን አያጠግብም አንድ ሃሳብ ብቻውን ዋጋ የለውም።በርካታ ሰዎች ከተባበሩ እራሳቸውን ሊያሻሽሉና መብታቸውን ሊያስከብሩ ባላጋራቸውን ሊያሸንፉ ሊያጠቁ ይችላሉ።ስራቸውም እንደ አንዷ ጤፍ ሳይሆን እንደምንበላው እንጀራ አንጀት አርስ ይሆናል።

እናስ ምነው የአገራችን ፓርቲዎች ይሄንን ጠላት በህብረት አናስወግድም? ህብረትን አንጥላ ተባብረን ወያኔ የሚባለውን ጠላት እናውርድ ።ወገን ለምን ይለያያል?አገር እኮ የጋራ ናት።ስለዚህ የወያኔን እኩይ ድርጊት የምንታገለው ስንተባበር ነው።

በዘመናችን በወያኔ አማካኝነት የከፋፍለህ ግዛ ያረጀ ያፈጀ መርህ ሲተገበር እናያለን።ብሔሮችና ብሔረሰቦች እንዲሁም የተለያዩ የሃይማኖትና እምነት ተከታዮች እርስ በርስ ከመከባበር ይልቅ የሚቆራቆሱባት አገር የሆነችውን አገራችንን ለመታደግ ፀሯ የሆነውን የወያኔ ስርዓት በተባበረ ክንድ ለማስወገድ ተባብረን እንስራ።" ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" ነውና ብሒሉ!

# "ወያኔ-ኦ-ሚሊኒየም" ኦፕሬሽን በጀግኖች ልጆቿ ከሸፈ

**Wondosen Lisanwork/ Gießen**

በግንቦት 7 ፀሐፊ እና ሕዝባዊ ኃይል አመራር አባላት ላይ የተቃጣው ረዥም ጊዜ የወሰደ የግድያ ሴራ ከሸፈ ። ይህ ሴራ የወያኔ የስለላና የግድያ ኃላፊዎች በሆኑት ጌታቸው አሰፋ እና ጸጋየ በርሄ የቅርብ ክትትል የተመራ፤ የአሻንጉሊቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሣለኝ እውቅናና ይሁንታ የተሰጠው፤ ወያኔ ከፍ ያለ ተስፋ የጣለበት ሴራ ነበር።

"ወያኔ-ኦ-ሚሊኒየም" የተሰኘው ይህ በወያኔ የመጨረሻ ከፍተኛው አመራር የተመራው ሴራ ስለወያኔ ውስጣዊ አደረጃጀት ጠቃሚ መረጃዎችን ሰጥቶ አልፏል። ከዚህም በተጨማሪ የወያኔ ሹማምንት ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ያላቸውን ንቀት፤ ከአመት በኋላ ስለሚደረገው ምርጫ ውጤት፤ ለሰላዮቻቸው ስለሚሰጡት ጉርሻ መጠን፤ እና ሌሎችም በርካታ ጉዳዮች ተስፋ ከጣሉበት ቅጥረኛ ነብሰ ገዳያቸው ጋር ካደረጉት የስልክ ንግግሮች ለማድመጥ ተችሏል። ይህ ለበርካታ ጥናቶች በግብዓትነት ሊውል የሚችለውን በድምፁ ከስምንት ሰዓታት በላይ የሚፈጀው የስልክ ንግግር ቅጂ በሕዝባዊ ኃይሉ የመረጃ ክፍል አማካይነት ለሕዝብ በኢንተርኔት በነፃ ተለቋል። በአጋጣሚውም የወያኔ ገበና ተጋልጧል።

በአንፃሩ ደግሞ የግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል የተደራጀው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቢሆንም ምን ያህል ወያኔን እንቅልፍ እንደነሳ ተጨባጭ ማስረጃ ሆኗል። ይህ ለነፃነት ታጋዮች ከፍተኛ የስነልቦና ብርታት የሚሰጥ ነገር ሆኖ ተገኝቷል። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል የተቃጣበትን ጥቃት ከማክሸፍ በተጨማሪ የወያኔን ገበና ማጋለጥ በመቻሉ የመጀመሪያውን ሁነኛ ድል ተቀዳጅቷል።

# ፌዴራሊዝምን የሚፈራው ማነው?

**Mimi Habtemariam/ Kronach**

ኢሕአዴግ በቅርቡ የጀመረው የአብዬን ወደ እምዬ ጉንጭ አልፋ ክርክር ግልጽ አይደለም። የትኛው ፓርቲ ነው ፌዴራል ሥርዓት አያስፈልግም ያለው? እኔ እስከሚገባኝ ድረስ በአብዛኞቹ ፓርቲዎች መካከል ያለው ክርክር "ምን አይነት ፌዴሬሽን?" በሚለው ጥያቄ ላይ ነው እንጅ "ፌዴሬሽን ያስፈልጋል" በሚለው ላይ አይደለም። ይህ ክርክር ደግሞ ተገቢ ነው። ምክንያቱም አሁን ያለውን አወቃቀር ጥያቄ ውስጥ ለማስገባት ከበቂ በላይ ምክንያቶች አሉ። ለምሳሌ (ክልሎች የሚመሠረቱት በብሔረሰብ ዙሪያ ነው ከተባለ) ሐረሪ ክልል ሆኖ ሲዳማ ያልሆነበት ምክንያት ምንድነው? አገው በአማራ ክልል ውስጥ ልዩ ዞን ሲሆን ጉሙዝ ለምን በሌላ ክልል ተጠቃለለ? ወዘተ.

ትክክለኛው የፌዴራሊዝምን ጽንሰ ሃሳብ የሚቃወመው ወይም በኃሰኝነትና በነጥ ለመተካት የሚሞክረው ራሱ ኢህአዴግ አይደለም ወይ?በእኔ እምነት የፌዴራሊዝም ዋና ጠላት ገዢው የወያኔ ኢህአዴግ ስርዓት ነው።

ዋናው ጥያቄ ተቃዋሚዎች ከሕዝብ ጋር እንዳይገናኙ መንገዱን እየዘጋ፣ ወጣቶች የተቃዋሚ ፓርቲ አባል እንዳይሆኑ እያስፈራራ እንዴት አድርጎ ነው አማራጭ የላቸውም፣ ፌዴራሊዝምን ይፈራሉ መተካካትን አይሞክሩትም ለማለት የሚደፍረው? ይህ እኮ

ቅጥፈትን፣ ነውረኝነትን ለልጆቻችን ማስተማር ነው! እውነተኛው የፌዴራሊዝም ስርዓት በኢህአዴግ መቃብር ላይ ይሰፍናል!

## በአንድነት እንቁም

**Tigist Birko Tafa/Bad Soden -Salmünster**

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ መንግስት የኢትዮጵያን ሕዝብ በግፍ መግዛቱን የሚያቆመው በህብረት መቃወም ስንችል ነው፡፡ ወያኔን ከስልጣን ማውረድ ከቻልን ስደት ጭቆና ዘረኝነትና አድልዎ ይወገዳሉ። በምትኩ በሃገራችን ሃብት መጠቀም እንችላለን። የሃገር እድገት የሚኖረው ዘረኝነትና መከፋፈል ሲቆም ብቻ ነው ለስደታችን ትልቁ ምክንያት የሆነው የወያኔ በጭቆና የተሞላ የግፍ ስርአት ነውና፡፡

ከዚህ አስከፊ የጭቆና አገዛዝ ለመላቀቅ በየዘመናቱ ዜጎች የፍትህ ጥያቄ ማንሳታቸው አልቀረም ነገር ግን ጥያቄዎቻቸው በወንጀለኛነት እየተፈረጁ እነሱም የአምባገነኑ የጥቃት ሰለባ ሲሆኑ ኖረዋል ይኖራሉም። አምባገነኖች ግን የአፈና መረባቸውን ዘርግተው በማንአለብኝነት ሃገርን እያጠፉ ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል በዜጎች ላይ ያለ ርህራሄ እየፈጸሙ የሃገር ሃብት እየመዘበሩና እያስመዘበሩ የተሻለ ስርአት በመገንባት ላይ እንገኛለን ይሉናል፡፡ እንዲህ አይነቱን ሸፍጥ የፖለቲካ ውንብድና ካልሆነ በስተቀር ከቶ ምን ሊባል ይችላል?

ስለዚህ በፍቅር ስንተሳሰርና በአንድነት ስንተባበር የወያኔን አምባገነን መንግስት ለመጣል ይቀለናል።የወያኔን አገዛዝ የምንጥለው በህብረት ሆነን ስንታገል ብቻ ነው፡፡ ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

## ተጠያቂው ማነው?

**Alem Tarekegne Damta/ Gladenbach**

ዘረኛውና አምባገነኑ የኢትዮጵያ መንግስት ወገናችንን አሰቃይቶ ሳይወዱ የግድን አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብን ለስደት ዳርጎታል።

የወያኔ መንግስትን የሚቃወመውን ወይም መብቱን በሰላም የሚጠይቀውን ሰው ለእስራትና ለከባድ ስቃይ ስለሚዳረጉ በአገራችን ሰርተን በሰላም መኖር አልቻልንም።መሰረታዊ የዜግነት መብት የተነፈግን ሰዎች ነን!

መቼ ይሆን በነፃነት መኖርና መተንፈስ የሚቻለው ለዚህ ትውልድ መሰደዱና በእስር ቤት መማቀቅ ተጠያቂው ማነው ትላላችሁ? እንደኔ የወያኔ መንግስት ብቻ ነው! ነፃነትና ፍትህ ለህዝባችን ይሁን!

## አምባገነኑን መንግስታችን በአይሲሲ ፊት

**Berhanu Bayu/Schweinfurt**

ሰሞኑን አይሲሲ ያወጣው አምባገነኖችን በሚከሰው ዓለምአቀፍ ህግ ላይ አብዛኞቹ የአፍሪካ መሪዎች እንቅልፍ ማጣታቸው እሙን ነው።ምክንያቱ ደግሞ በአገራቸው ላይ እየፈፀሙት ያለው የአፈናና ግድያ እንዲሁም አገራቸውን ለግል ጥቅማቸው ስለሚያውሉት የአይሲሲን መርሆዎች በጋራ ሲቃወሙ መታዘብ ችለናል።

ከተቃዋሚዎቹ መካከልም የእኛው ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ አንዱ ናቸው።አብዛኞቹ የአፍሪካ መሪዎች እንደ ሰው ሆነው ተፈጥረው እንደነሱ እኩል የተፈጠረውን ክቡሩን የሰው ልጅ ሲገድሉና ሲያስሩ ሲያሰቃዩ ሲያሳድዱ ቅንጣት ታህል የማይሰማቸው ከመሆናቸውም በላይ ብዙ አረመኔያዊ ድርጊት እየፈፀሙ መቀጠል ስለሆነ አላማቸው እንዲሳካ አይሲሲን ላለመተባበር መማማል ይዘዋል።

አገራችን በደም በተጨማለቀች እጆችና በወንጀለኞች ስብስብ የምትመራ አገር በመሆኗ ሰሞኑን ጠ/ሚ ሃይለማርያም ደሳለኝ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ አንድነት እና ሰማያዊ ፓርቲዎች ያካሄዷቸውን ሰላማዊ ሰልፎች ሽብር አነሳሾች ናቸው በማለት በሚዲያ አውጀዋል።ስለዚህ የአምባገነኖችን አገዛዝ ለመገርሰስ አንድ ላይ በመሆን ህዝባችን በጉልበተኛ ሳይሆን በህግ የሚተዳደርበትን መንገድ ተባብረን መፍጠር አለብን።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

## ወያኔ የአገር ጠላት ነው

**Arsema Berhanu Tefera/ Röthlein**

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሰዎች ከፍተኛ የሰብዓዊ ረገጣ እየተደረገባቸው ይገኛል።ከሚኖሩበት ይፈናቀላሉ ገዢውን ፓርቲ ባለመደገፋቸውና በፖለቲካ አመለካከታቸው እንዲሁም የእምነት ነፃነታቸውን በመጠየቃቸው በህዝቦች ላይ እየደረሰ ያለውን አስከፊ መከራ ለዓለም ህዝብ በማሳወቃቸው በመፃፋቸው ምክንያት በእየእስር ቤቱ በመማቀቅና በመሞት እንዲሁም በመሰቃየት ላይ ይገኛሉ።

ስለዚህ ይህ ነገር እስከመቼ ይቀጥላል? ውድ ኢትዮጵያውያንና የህዝቦች ስቃይና መከራየሚሰማችሁ ሁሉ ይህንን ጨካኝና አረመኔ መንግስት ልንቃወመው ልናወግዘውና በአደባባይ ልንታገለው ይገባል።

እኛም ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነን ልዩነታችንን ወደጎን ትተን ስርዓቱን ተባብረንና ተደጋግፈን በቃህ ልንለው ይገባል!ስለዚህ ዛሬ ነገ ሳንል በአንድ አቅጣጫ ባንድነትና ባለንበት ትግላችንን አጠናክረን መቀጠል አለብን።አምባገነኑ የኢትዮጵያ መንግስት እስኪወድቅ በፅናት በትዕግስት መቆም አለብን።ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

# የአማራ ህዝብ ስቃይ እንዲያበቃ መስዋዕትነት እንክፈል

**Yohanes Samson/Bad Hersfeld**

ወያኔ ከነፀረ-አማራ ፖሊሲው በስልጣን እስካለ ድረስና በአማራ ስም አማራውን እያፈኑ እየሰለሉ ከወያኔ ፍርፋሪ እየለቀሙ ለመኖር የቆረጡ ከአማራው መሃል የወጡ ከሃዲዎች አማራውን መቆጣጠር እስከቻሉ ድረስ የአማራ ህዝብ መራቆት ስደት ውርደት ሰቆቃና ሞት የማይለዩት ህዝብ እንደሆነ ይቀጥላል።

እኛ ህዝባዊ ሃይሎች በእብሪትና በጥላቻ የተሞላ በወያኔ የሚፈፀም በአማራ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ማስቆም የሚቻለው በጠመንጃና በተባበረ የህዝብ አመፅ ብቻ ነው-ብዬ አምናለሁ።ከንፈር መምጠጥ ዋይታ ኡኡታ ጋዜጣዊ መግለጫ ወያኔ የአማራን ህዝብ ቅስም ለመስበር የዘረጋውን መርሃግብር እንዲያጥፍ አያደርገውም።

ወያኔ ትዕግስትን እንደ ፍራቻ አርቆ አሳቢነትን እንደሞኝነት የሚቆጥር በአማራው ላይ ቂምና ጥላቻን ሰንቆ የተነሳ ድርጅት ነው።ስለዚህ ድርጅቱ ማንም ምንም አያደርገኝም በሚል ትምክህት ተወጥሮ የሚያደርገውን ፀረ-ህዝብ ዘመቻ ማክሸፍ ይገባናል።ከእንዲህ አይነቱ በራሱ ፕሮፓጋንዳና ከንቱ ውዳሴ ከሰከረ ድርጅት ጋር የሚደረግ ትግል ያለምንም መወላወል ከፍተኛ እልህና ውሳኔን ይሻል።ከወያኔ ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጠው ገድለው ለመሞት የቆረጡ የወገን ደም መላሾችን ይጠይቃል።ቤታቸውን ዱርና ገደሉን አድርገው ወተት ይሸፍታል እንኳንስ ሰው ሲበደል የሚሉ ቁጡዎችን ይፈልጋል።

ሌላው ሁሉ አማራጭ ተፈትሿል ተሞክሯል ታይቷል።የቀረው አንድ ምርጫ ብቻ ነው- መስዋዕትነት! በአገዛዙ የከፋህ የመረረህ የተበደልክ በቃኝ ያልክ ተሰባስበህ በወያኔ መቃብር ላይ አዲሲቷን ኢትዮጵያ እንገንባ! ድል በወያኔ ለሚረገጡ ኢትዮጵያውያን በሙሉ!

## ወንድሜ አንሳኝ!

ዉጣ ውጣ ብለው፣ አስወጡት በግዱ፣
ያገሩ ጎዳና፣ ቢጠፋው መንገዱ::

በሬው ጥጃ ወልዶ፣ ተኝቶ ይልሳል፣
አረብ ባምላክ ቢሉት፣ መቸ ይመለሳል::

ኸረ እዩልኝ ጎበዝ፣ እዩልኝ ወገኔን፣
አጋድመው ቢረግጡት፣ አመመኝ ቀኝ ጎኔን::

እህ ብለው ብለው፣ አንገቴ ደረሰ፣
አክ ብለው ወጣ፣ ደም እየለበሰ::

የወገኔ ስቃይ፣ እረፍት እየነሳኝ፣
አዙሮ ጥሎኛል፣ እስኪ ወንድም አንሳኝ::

**Wondosen Lisanwork/Gießen**

# ለምን ተዋረድን?

**Betewedaj Adenew/ Bayreuth**

የአንድ ሀገር መንግስት ዜጎቹ እየተደፈሩ፣በማጎሪያ ካምፕ በረሀብና በውሃ ጥም፣ሌላው ቢቀር መጸዳጃ ቤት እንኳ ተከልክለው ፍጹም ከሰውነት ክብራቸው ወርደው እየተበደሉ፣እየተገደሉ ባለበት ወቅት ገና ለገና በሰልፍ ላይ በሚንጸባረቅ ጥላቻና ተቃውሞ የዲፕሎማሲ ግንኙነቴ ይበላሽብኛል ብሎ መናገር ይችላል? ሌላው ይቅር አንድ ክፉና ደጉን የለየ ሰው የሚያስበው ጤነኛ ሃሳብ ነው ማለትስ ይቻላል?::


ከእገዳው ባሻገር የሚደንቀው ነገር ደግሞ በዜጎቻችን ላይ የተደረገው ድብደባ ነው፣የሆነ ማስተላለፍ የፈለጉት ነገር ያለ ይመስላል፡፡የጭካኔያቸውን መጠን እንድናውቅ -የሚደበድቡት አቅመ-ደካሞችን፣ሽማግሌዎችንና ሴቶችን እየመረጡ በፍጹም አረመኔነት ነበር፡፡ይህን ተግባራቸውን ስመለከት የደረሱበትን የዝቅጠት ደረጃ መታዘብ ችያለው፡ እናንተየ መንግስት ቢኖረን ኖሮ ይሄ ሁሉ ውርደት ይፈጸምብን ነበር?

# ለመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ መንግስት አለ ወይ?

**Abenezer Ahmed Behailu/Hof**

ሰሞኑን ከተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እንዳየነውና እንዳደመጥነው ኢትዮጵያውያን በሳውዲ አረብያ እየታረዱ፣እየተደፈሩ እና እየተደበደቡ ሲሆን የወያኔ መንግስት ግን ይህንን የሳውዲ አረቢያን ድርጊት በአደባባይ ለመኮነን ሞራልም ድፍረትም ከማጣቱ በላይ በሀገር ቤት የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ይህንን ድርጊት ህዝብን በማስተባበር በአደባባይ ለመቃወም ሲወጡ ሳውዲዎች በዜጎቻችን ላይ ከፈፀሙት ጭካኔ በማይተናነስ መልኩ ዜጎቻችንን የደበደበና ያሰረ ሲሆን ዛሬ የሳውዲ አረቢያ ካምፓኒዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በአስር ሺዎች ካሬ ሜትር የሚለካ መሬት እዚህ ግባ በማይባል ዋጋ ወስደው የሩዝ እና ፍራፍሬ ምርቶችን በማምረትን እና በቀጥታ ወደ ሀገራቸው በመላክ የምግብ ፍጆታቸውን ሲሸፍኑ የኛ ዜጎች ግን በላባቸው ያፈሩትን ንብረት በሃይል ተቀምተውና ሰብዓዊ ክብራቸው ተገፎ ከሀገር እንዲወጡ እየተደረገ ይገኛል።

ለመሆኑ ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ አለ ወይ? መልሱ የለም ሲሆን ስለወገኖቹ የሚቆረቆር ኢትዮጵያዊ መንግስት ለመመስረት በጋራ እንታገል!!!




Demo crazy

**Source:- ethiopianreview**



# ህዝቡን የሚሸጥ መንግስት

**Eden Dawit/ Gießen**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራችን በኢትዮጵያ በከፋ ሁኔታ እየተካሄደ ያለው የወጣት ሴቶችና የወጣት ወንዶች ሽያጭ በዓለም አንገታችንን እንድንደፋ አድርጎናል።

ዜጎቻችን በየጊዜው በየሃገሩ ድንበር በሽፍቶችና በዘራፊዎች ህይወቱን የሚያጣው ህዝብ ቁጥር ስፍር የለውም ይህም ሆኖ በሌላ መንገድ መንግስት ተብሎ በቦታው የተቀመጠው አሻንጉሊት አንድ የሃገር አስተዳዳሪ ከሚያደርገው ተግባር የተለየና ከሌሎች ዘራፊዎች ባልተለየ መልኩ ህዝቦቹን ህጋዊ በሚል ሽፋን ሕይወታቸውን አደጋ በሚጥል ሁኔታ በመሸጥ ላይ ይገኛል።

ቤተሰቦቻቸውን ነገ የተሻለ ለማድረግ በአገራቸው ያለው የመንግስት በደልና ጭቆና ምክንያት አልሳካ ቢላቸው ካለው የባሰ መርጠው ሄደዋል።

በዚህም ምክንያት በየደረሱበት እንደባሪያ እየተቆጠሩና እየተረገጡ ህይወታቸውንም እያጡ ይገኛሉ።

ዛሬ ኢትዮጵያ ማለት ዘመናዊ የባሪያ ንግድ የሚካሄድባት መስላለች። ልጆቿም በስቃይ በየቦታው ሞታቸውን በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ።ታዲያ ወገኖቼ በዚህ ሁኔታ እንዴት ይቀጥላል።ይሄን አገር አዋራጅና አገር ሻጭ መንግስት ተባብረን ልንጥለው ይገባናል!በአንድ ከተነሳን ምንም የሚከብድ የለም።ለዚህም ትግላችን ኢህአፓ ከጎናችን ሆኖ ትግላችንን ያግዛል።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።

# በሳውዲ ለሚደርሰው እልቂት የወያኔ መንግስትም ተጠያቂ ነው።

**Yohannes Selamu Benti /Hof**

ሰሞኑን በሳውዲ አረቢያ በዜጎቻችን ላይ ለተፈፀመው እልቂት የወያኔ መንግስትም ከተጠያቂነት አያመልጥም።

የወያኔ ፖሊሲ ወጣቱን ያላቀፈ በመሆኑና በወጣቱ ላይ የተለያዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች የሚደርስበት በመሆኑ ሀገሩን ጥሎ የሚሰደድ ሲሆን በዚያም ስቃይና እንግልት እየደረሰበት ይገኛል።ይሁን እንጂ የወያኔ መንግስት በጅዳ የሚገኘውን የቆንስላ ጽ/ቤት በመዝጋት ወገኖቻችን መንግስት አልባ መሆናቸውን በግልጽ ከማሳየቱም ባሻገር ሰማያዊ ፓርቲ ይህንን የሳውዲ አረቢያ መንግስትን ለማውገዝ በአዲስ አበባ በሚገኘው የሳውዲ ኤምባሲ ፊትለፊት ሰላማዊ ሰልፍ ቢጠራም ቅጥረኛው የወያኔ መንግስት የፌደራል ፖሊሶችን በማሰማራት ለሰልፍ የወጡ ሰላማዊ ሰዎችን በመደብደብና በማሰር ሰልፉን አስተጓጉላል።

በሀገራችን ነጻነትና ዴሞክራሲ እስካልሰፈነ ድረስ በዜጎቻችን ላይ የሚደርሰው እንግልትና ስቃይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ እንደሚሄድ ግልጽ ነው በመሆኑም የወያኔን መንግስት በማስወገድ ዜጎች በሀገራቸው ላይ በነፃነት የሚኖሩበትን ዕድል ለመፍጠር በጋራ እንነሳ።




Funny Joke
Source:- **facebook**

# እውን ኬኔዲን ማን ገደላቸው?

Dawit Fanta
Tila Magazine Editor in Chief
/ Frankfurt, Germany

## መልሱን ለማግኘት የተቃረበ ሐተታ ይዘናል!



**"በርሊናዊ ነኝ /ICH BIN EIN BERLINER/"** *"ከሁለት ሺህ አመታት በፊት ሰዎች በኩራት ሮማዊ ነኝ ይሉ ነበር፤ ዛሬ ደግሞ በነፃው ዓለም የምንገኝ ሰዎች በኩራት በርሊናዊ ነን እንላለን"* ጁን 26, 1963 ከዛሬ ሃምሳ አመት በፊት 35ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆን ፊዝጄራልድ ኬኔዲ ነበሩ በበርሊን ለተሰበሰቡ የምዕራብ ጀርመን ዜጎች የተናገሩት። እኚህ ባለራዕይና የሰላም ሰው ከዚህ ታሪካዊ ንግግራቸው በኋላ በህይወት የቆዩት ለ 5 ወራት ብቻ ነበር።ያውም በአደባባይ ነበር የተገደሉት።

ኖቬምበር 22, 1963 ዓ.ም. ኬኔዲ ባለቤታቸውን ጃኩሊንን እንዲሁም ምክትል ፕሬዝዳንቱን ሊንደን ቢ. ጆንሰንን በማስከተል ወራት ብቻ ለቀረው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ቅስቀሳ ለማድረግ ወደ ቴክሳሷ የዳላስ ከተማ በተዘጋጀላቸው ግልጽ ሊሞዚን ሆነው በህዝብ መካከል እየተጓዙ ሳለ ነበር "ዲሌይ ፕላዛ" በመባል በሚታወቀው አደባባይ ላይ ሲደርሱ ጭንቅላታቸውንና ጉሮሯቸውን በሁለት ጥይት ተመትተው የሞቱት።በወቅቱ የዳላስ ፖሊስ ሊ ሃርቬይ አስዋልድ የተባለ የቀድሞ የባህር ኃይል ሬዳር ኦፕሬተርን በቁጥጥር ስር ሲያውል ይህ ግለሰብ አፍቃሬ ኮሙዩኒስት ከመሆኑ ባሻገር በአሜሪካ ታሪክ የመጀመሪያው በሆነ ሁኔታ በ1959 ዓ.ም. ለሶቭየት ህብረት መንግስት እጁን በመስጠት ጥገኝነት ጠይቆ የነበረ፥ከሁለት አመት በኋላም ራሺያዊት ሚስት አግብቶ ወደ አሜሪካ የተመለሰ፤እንዲሁም "Fair Treatment for Cuba" በሚል አሜሪካ በኩባ ላይ ያላትን ፖሊሲና አቋም በግልጽ ከሚተቹ ቡድኖች ጋር የሚንቀሳቀስ ግለሰብ ነበር።ከዚህ በኋላ አስዋልድ በህይወት የቆየው ለሁለት ቀናት ብቻ ነበር። ያውም በፖሊስ ጣቢያ ግቢ በፖሊስ እንደታጀበ በቀጥታ ስርጭት በቴሌቪዥን እየታየ ወደ ፌደራል ማረሚያ ሊወሰድ ሲል ነበር ጄምስ ራቢ በተባለ ግለሰብ በጥይት ተመትቶ የተገደለው።አስዋልድ ከመገደሉ ጥቂት ሰከንዶች ቀደም ብሎ በወቅቱ ግራና ቀኝ ለነበሩ ጋዜጠኞች "I'm a patsy" ብሎ ነበር።ይህም ማለት እውነተኛው ገዳይ እኔ አይደለሁም በኔ ተሳበበ እንጂ እንደማለት ሲሆን ራቢም አስዋልድን በመግደል ምስጢሩን የተደበቀ ሆኖ እንዲኖር ሲያደርገው የራቢ አሟሟትም ከሚነገረው ባሻገር ግልጽ አይደለም። በእርግጥ በተጨባጭ ኬኔዲን እከሌ የሚባል ቡድን ወይም ሀገር አስገደላቸው ማለት ከባድ ቢሆንም በሶስት ዓመት የፕሬዚዳንት ዘመናቸው ያፈሯቸውን ጠላቶችና የፀባቸውን ጥልቀት መፈተሹ ማን አስገደላቸው ወደሚለው አቅጣጫ ይመራናል።

1. **ኩባ**፡- ፊደል ካስትሮ የባፕቲስታን መንግስት በ1959 ኢ.ም በመገልበጥ ስልጣን ሲይዙ በአሜሪካውያን ባለቤትነት የተያዙ ሰፋፊ የትምባሆ እርሻዎችን በመውረሳቸው ከአሜሪካ ጋር አይንና ናጫ መሆን ጀመሩ። በዚህም ሳይበቃ የአሜሪካ ሁኔታ ያሰጋቸው ካስትሮ የኮሚኒስቱን ጎራ በሰፊው ተቀላቀሉት።

በመሆኑም የአሜሪካ መንግስት የካስትሮን መንግስት ለመጣል የተለያዩ አማራጮችን የተጠቀመ ሲሆን "The Bay of Pigs Fiasco" በመባል የሚታወቀው ያልተሳካ ዘመቻ ካስትሮንና ኬኔዲን ሌላ ውጥረት ውስጥ የከተተ ሲሆን በ1962 ዓ.ም. ራሺያ መካከለኛ ርቀት የሚጓዙ ኒውክሌር ተሸካሚ ሚሳኤሎችን በኩባ (ኩባ ከአሜሪካዋ የፍሎሪዳ ግዛት 90 ማይል ብቻ የምትርቅ መሆኗን ልብ ይሏል) መትከል በመጀመሯ የአሜሪካ ባህር ኃይል ሙሉ በሙሉ ኩባን በመከበብ ከራሺያ ወደኩባ እየመጡ ከነበሩና የኒውክሌር ሚሳኤል ከጫኑ የራሺያ መርከቦች ጋር ፍጥጫ ውስጥ የገቡበት ወቅት ሲሆን በኬኔዲና በራሽያው መሪ ኒኪታ ክሩስቾቭ መካከል ለ 11 ቀናት በተደረገ ድርድር ራሺያ የሚሳኤል ግንባታውን ወዲያው ስታቋርጥ በምላሹ የኬኔዲ አስተዳደር አንድ ይፋ የሆነና አንድ ግን ለሰላሳ አመታት ያህል ለህዝብ ይፋ ያልተደረገ ድርድርን አድርጓል። ኩባን በኃይል እንደማይወሩ ኬኔዲ ለራሺያ እና ለዓለም ህዝብ ይፋ ሲያደርጉ በምስጢር ከራሺያ መንግስት ጋር በመነጋገር አሜሪካ ቱርክ ላይ ተክላ የነበረውን "ጁፒተር" በመባል የሚታወቁና ራሺያን መምታት የሚችሉ ሚሳኤሎችን በስድስት ወራት ጊዜ ለማንሳት ነበር።

ከላይ የተዘረዘሩት ክስተቶች በሁለቱ ሀገራት መሪዎች መካከል ውጥረትንና ጥላቻን ያባባሰ ቢሆንም ካስትሮ ኬኔዲን ለማስገደል የሚያደርስ እብደት የለባቸውም። ካስትሮ ይህንን አይነት እብደት ሞክረውት ቢሆን ኖሮ ዛሬ ኩባ የምትባል ሀገር መኖሩ በራሱ አጠያያቂ ሊሆን እንደሚችል በ2006 ዓ.ም. ራሳቸው ካስትሮ ጄሲ ቬንቱራ ለተባለ የሚኒሶታ የቀድሞ ገዢ ለነበረ ሰው ሃቫና ውስጥ መግለፃቸውን "American Conspiracies" በተሰኘ መጽሐፉ ገልጿል።

2. **እስራኤል፡-** የጆን ኤፍ ኬኔዲ አባት ጆሴፍ ኬኔዲ የሚባሉ ሲሆን ከ1938-1940 ዓ.ም ድረስ በእንግሊዝ የአሜሪካ አምባሳደር ሲሆኑ ከመንግስታቸው አቋም በተፃራሪ የሂትለር አድራቂና የናዚ ፖሊሲዎችን የሚደግፉ ነበሩ።ነገር ግን ኬኔዲ ለፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ሲወዳደሩ በአሜሪካ ከሚገኙ አይሁዳውያን ጋር በመደራደር ለምርጫ ቅስቀሳ የገንዘብ ድጋፍ እንዲሁም የአሜሪካ አይሁዳንን ድምጽ ያገኙ ሲሆን ኬኔዲም በመካከለኛው ምስራቅ የሚኖራቸው አቋም የእስራኤልን ጥቅም እንደማይፃረር ቃል ገብተውላቸው እንደነበር ማይክል ኮሊንስ ፒፐር "The Final Judgement" በተሰኘ መጽሐፉ ውስጥ ይጠቅሳል።ይሁንና ኬኔዲ ወደስልጣን ከመጡ በኋላ ከሳቸው በፊትም ይሁን ከሳቸው በኋላ ከመጡ የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች በተለየ ሁኔታ የመካከለኛው ምስራቅን ሁኔታ ለአረቦችም የተሻለ ዕድል እንስጣቸው በማለታቸው ከፈረንሳይ በቅርብ ነፃነቷን ከተጎናፀፈችው አልጄሪያ ጀምሮ ሌሎች የአረብ አገራትም በኬኔዲ ላይ ከፍተኛ ተስፋና እምነት ሲጥሉ እንደ አዲስ ከተመሰረተች ሁለት አስርት አመታትን ላላስቆጠረችው እስራኤልና የቤንጎሪዎን አስተዳደር የማይወጡት ፈተና ሆነባቸው።

ከዚህ ጎን ለጎን እስራኤል በኔጌቭ በረሃ የዲሞና የኒውክሌር ፋሲሊቲ መገንባቷን ለሰላማዊ ጥቅም ነው ብትልም ኬኔዲ በአሜሪካ ባለሙያዎች ከፍተኛ ፍተሻ እንዲደረግ ከማዘዛቸውም በላይ ቤንጎሪዮን ኬኔዲን በግል ለማግኘት በርካታ ጊዜ ሞክረው ኬኔዲ ፈቃደኛ ካለመሆናቸው ባሻገር አሜሪካ ኒውክሌርን ለወታደራዊ ግልጋሎት ለሚጠቀሙ ሀገራት እርዳታ አልሰጥም ያለችውን ህግ በእስራኤልም ላይ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ኬኔዲ መግለፃቸው በቤንጎሪዮን መንግስትና በሞሳድ ጥርስ ውስጥ እንዲገቡ ሲያደርጋቸው ቤንጎሪዮን በተለያየ ጊዜ "የእስራኤል ህልውና አደጋ ላይ ወድቋል" እያሉ ኬኔዲን ከማማረር አልፈው በጁን 1963 ዓ.ም እስራኤልን እንደሀገር ካቋቋሙበትና ለ15 አመታት በጠቅላይ ሚንስትርነት ካገለገሉበት ስልጣናቸው ለቀዋል።አስገራሚው ነገር ኬኔዲ በእስራኤል የኒውክሌር ግንባታ ላይ ያላቸውን ጠንካራ አቋም ለመግለፅ ለተተኪው ጠቅላይ ሚንስትር ሌቪ ኤሽኮል በጁላይ 05, 1963 ዓ.ም. ደብዳቤ የፃፉ ሲሆን በእስራኤል በኩል የኬኔዲ በሥልጣን መቆየት እስራኤል ላሰበቸው የኒውክሌር ጦር ግንባታ ትልቅ ጋሬጣ እንደሆነ የታመነበት ጊዜ እንደነበር ይገመታል።

3. **ሲ.አይ.ኤ.**፡-የአሜሪካው የስለላ ተቋም "ሲ.አይ.ኤ" የሚለውን ስያሜ ይዞ በ1947 ዓ.ም. በላንግሌይ ቨርጂኒያ የተቋቋመ ሲሆን በማርች 1954 በኔሽናል ሴኩዩሪቲ ካውንስት ዳይሬክቲቭ ቁጥር 5412 መሠረት "እልል በቅምጤ" የሚያስብል ትልቅ ስልጣን ተሰጠው።በዚህ መመሪያ መሰረት ሲ.አይ.ኤ ምስጢራዊ ዘመቻዎችን (Covert Operation) በበላይነት እንዲመራ፤በዚህም የጦር ኃይሉ እገዛ ሲያስፈልገው ጦሩን በማዘዝ ትላልቅ ጦርነቶችን ማድረግ የሚያስችል ስልጣን አገኘ።ስለሆነም በሲ.አይ.ኤ መሪነት በአይዘናወር (ከኬኔዲ በፊት የነበሩት 34ኛው ፕሬዝዳንት) ዘመን ታቅዶ በኬኔዲ የስልጣን ዘመን የተካሄደውና ያልተሳካው የ"ቤይ ኦፍ ፒግስ" ዘመቻ ገና ወደስልጣን ከመጡ አራት ወራት ብቻ ለሆናቸው ኬኔዲ ከውጭም ከውስጥም ከፍተኛ ተቃውሞ ማስከተሉ ኬኔዲ በሲ.አይ.ኤ ላይ ጥርሳቸውን እንዲነክሱ ከማድረጉ በላይ የሲ.አይ.ኤ ዳይሬክተር የነበረውን ኤለን ዳላስን ከስራ ሲያባርሩ በሂደትም በኔሽናል ሴኪዩሪቲ አክሽን ሜሞራንዳ ተራ ቁጥር 55፣56 እና 57 (National Security Action Memoranda / NSAM/ #55,56&57) መሰረት ሲ.አይ.ኤን ጥርስ የሌለው አንበሳ ሲያደርጉት በተለይ በ NSAM #55 መሰረት ሲ.አይ.ኤ በ1954 ዓ.ም አግኝቶት የነበረውን ሥልጣን በመንጠቅ ለጆይንት ቺፍ ኦፍ ስታፉ በመስጠታቸው ሌላ የተኛ አንበሳን በቁጣ እንዲነሳባቸው አደረጉ፡- ''ሚሊተሪ ኢንደስትሪያል ኮምፕሌክስ"።

"ሚሊተሪ ኢንደስትሪያል ኮምፕሌክስ" የሚለውን ለመጀመሪያ ጊዜ ለህዝብ ይፋ ያደረጉት 34ኛው ፕሬዚዳንት ጄነራል ድዋይት አይዘናወር ሲሆኑ በጃንዋሪ 17, 1961 ዓ.ም የስንብት ንግግራቸው ላይ ይህ "ሚሊተሪ ኢንደስትሪያል ኮምፕሌክስ" በአሜሪካውያን ነፃነትና ዴሞክራሲ ላይ የተደቀነ ትልቅ ፈተና መሆኑን ገልፀው ነበር። ለመሆኑ ''ሚሊተሪ ኢንደስትሪያል ኮምፕሌክስ" ምን ማለት ነው?ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ በቀጥታ ወደ ትርጉሙ ከመግባታችን በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች እናንሳ።የአሜሪካ መንግስት የጦር መሣሪያዎችን በመንግስት ደረጃ የማያመርት ሲሆን ከግዙፎቹ "ቢ-52" የጦር ጀቶች እስከ እጅግ ዘመናዊው ''ቢ-2 ስፒሪት"፣ከቶም ሃውክ ክሩዝ ሚሳኤሎች እስከ ግዙፎቹ ኒሚትዝ ክላስ የጦር ጀት ተሸካሚ መርከቦች ድረስ በግለሰቦች በተያዙ ኮርፖሬሽኖች የሚመረቱ ሲሆን መንግስትም ግዢውን የሚፈፅመው ከነዚህ ኮርፖሬችኖች ነው። እናም "ሚሊተሪ ኢንደስትሪያል ኮምፕሌክስ" ማለት በአሜሪካ መከላከያ ሚንስቴር መ/ቤት ፔንታጎን፣ በጦር መሣሪያ አምራች ኮርፖሬሽኖችና በአሜሪካ የህግ አውጪ አካላት መካከል ያለ የጥቅም ትስስር ማለት ነው።የህግ አውጪው አካል የውጭ ፖሊሲውን ጦርነት መር እንዲሆን ካደረገ ፔንታጎን የግድ የጦር መሣሪያ ከነዚህ ኮርፖሬሽኖች ይገዛል ማለት ነው። እናም NSAM #55 ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ሲ.አይ.ኤ ለ"ሚሊተሪ ኢንደስትሪያል ኮምፕሌክስ" ወርቅ የምትጥል ዶሮ ማለት ነበር።ኬኔዲ በዚህ ሳይወሰኑ ኔሽናል ሴኪዩሪቲ አክሽን ሜሞራንደም ቁጥር 263 (NSAM #263) የሚል መመሪያ ሲያወጡ ይህም በቬየትናም የሚገኘውን የአሜሪካን ጦር ማስወጣት የሚል ነበር።

ወርቅ የምትጥል ዶሯቸው (ሲ.አይ.ኤ) በ NSAM #55 ለታረደባቸው "ሚሊተሪ ኢንደስትሪያል ኮምፕሌክስ" NSAM #263 በቀጥታ ወደነሱ የተወረወረ የመግደያ ጦር እንደሆነ ተረድተውታል። ኬኔዲ NSAM #263ን ያፀደቁት ከመገደላቸው አንድ ወር ቀደም ብሎ የነበር ሲሆን በዚህ ወቅት በሲ.አይ.ኤ እና በኬኔዲ መካከል ውጥረቱ ጫፍ ላይ ከመድረሱም ባሻገር ታዋቂው ጋዜጠኛ አርተር ክራክ አክቶበር 03, 1963 ዓ.ም. በወጣው ኑዮርክ ታይምስ መፅሔት ላይ "Intra-Administration War in Vietnam" በሚል ርዕስ በፃፈው ፅሑፉ ውስጥ ከአንድ ትልቅ የመንግስት ባለስልጣን አገኘሁት በማለት የሚከተለውን ዘገባ ይዞ ወጣ፡- "ሲ.አይ.ኤ ከኬኔዲ አስተዳደር ቁጥጥር ውጪ እየሆነ ከመምጣቱም ባሻገር በአሜሪካ ታሪክ መፈንቅለ መንግስት የሚካሄድ ከሆነ ይህንን የሚፈፅመው ጦር ሰራዊቱን የሚመራው ፔንታጎን ሳይሆን ሲ.አይ.ኤ ነው" ሲል

ገለፀ።ማርክ ሌን "ፕላውዝብል ዲናያል/ Plausible Denial/" በተሰኘው መፅሐፉ ጋዜጠኛ አርተር ክራክ ለኬኔዲ ካለው መቀራረብ አንፃር "ከፍተኛ ባለስልጣን" ተብለው የተጠቀሱት ራሳቸው ኬኔዲ ናቸው ጉዳዩንም በሂደት ወደ ህዝብ ለማድረስ የተጠቀሙበት መንደርደሪያ ነው ሲል ይሞግታል።ያም ሆነ ይህ ኬኔዲ በህዝብ ተወዳጅ ከመሆናቸው አንፃር ቀጣዩንም ምርጫ በስልጣን እንደሚቆዩ ግልጽ የነበር ሲሆን የኬኔዲ በስልጣን መቆየት "ህልውናችን አደጋ ላይ ወደቀ" ከሚሉት ጀምሮ "ጥቅማችን ተነካ" እስከሚሉት ድረስ በአንድ የሴራ ጠረጴዛ ዙሪያ እንዲሰበሰቡ ሳያደርጋቸው አልቀረም።በርግጥ ይህንን ለማለት በኬኔዲ ሞት ማግስት የተደረጉ ለውጦችን መመልከቱ በቂ ነው።ከዛ በፊት ግን ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ኬኔዲ ያወጧቸው መመሪያዎችም ሆኑ በእስራኤል ላይ የያዙት አቋም የአስተዳደራቸው ጭምር እንጂ የሰውየው የግል አቋም ብቻ አልነበረም።ስለሆነም የኬነዲን ሞት ተከትሎ ስልጣኑን የያዙት ሊንደን ጆንሰን (በኬኔዲ ጊዜ ምክትል ፕሬዝዳንት የነበሩ ሲሆን ኬኔዲ እንደተገደሉ በዚያው ዕለት የአሜሪካ ህግ የስልጣን ክፍተት እንዳይኖር ስለሚያስገድድ ቃለ መሃላ በመፈፀም ፕሬዚዳንት ሆነዋል) ቢያንስ የኬኔዲ የስልጣን ዘመን እስኪያልቅ (ወራት ብቻ መቅረቱን ልብ ይሏል!) የነበረውን አስተዳደር ውሳኔ ማስፈፀም ይጠበቅባቸዋል።ነገር ግን የኬኔዲ ካቢኔ የስልጣን ዘመን ሳይፈፀም የኬኔዲን ሞት ተከትሎ መንበረ ፕሬዚዳንቱን ጆንሰን ስለተቆጣጠሩት ብቻ የሚከተሉትን አስደማሚ ለውጦች በአጭር ጊዜ ሲያደርጉ በርካታ በኬኔዲ ሞት ላይ ጥናት ያደረጉ ሰዎች ጆንሰንም የሴራው አካል ሳይሆኑ እንዳልቀሩ ይተነትናሉ።

ጆንሰን በኬኔዲ አስተዳደር ጊዜ ሲ.አይ.ኤን ጥርስ የሌለው አንበሳ ያደረገውን NSAM #55፣56 እና 57ን የሚሽረውንና ሲ.አይ.ኤን ወደቀድሞ ስልጣኑ የሚመልሰውን አዋጅ NSAM #273 ያፀደቁት ኬኔዲ በተገደሉ በአራተኛው ቀን (ቀን እንጂ ወር




አላልኩም!!!)ሲሆን የ "ሚሊተሪ ኢንደስትሪያል ኮምፐሌክስ"ን አከርካሪ ሰብሮ የነበረውንና የአሜሪካንን ጦር ከቬትናም ለማስወጣት የፀደቀውን NSAM #263 በመሻር በማርች 1964 ዓ.ም. (ኬኔዲ በተገደሉ በአራተኛ ወራቸው) NSAM #288ን ሲያፀድቁ በቬትናም የሚገኘው የአሜሪካ ጦር ቁጥር ከሃያ ሺህ ወደ ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ሲያድግ ዘመቻውም ከስውር ዘመቻ ወደ ሙሉ ጦርነት አድጓል።በዚህ ጦርነት የአሜሪካ መንግስት ስድስት ትሪሊየን ዶላር ወጪ ሲያደርግ አብዛኛው ገንዘብ ወደ "ሚሊተሪ ኢንደስትሪያል ኮምፐሌክስ" ካዝና ገቢ ሆኗል።ሌላው ጆንሰን ከኬኔዲ አስተዳደር በተለየ የእስራኤልን የዲሞና ኒውክሌር ግንባታ ዞር ብለው ያላዩ ሲሆን ይባስ ብለው ቀድሞ ከነበሩት መንግስታት በተለየ የሦስት ጊዜ እጥፍ የገንዘብ እርዳታ ሲያደርጉ ለመጀመሪያ ጊዜ በቁጥር በርካታ የሆኑ ሚሳኤሎችንና የጦር መሳሪያዎችን በገፍ ለእስራኤል በእርዳታ መልክ ሲሰጡ ችለዋል። የኬኔዲን ሞት ለማጣራት መንግስት አጣሪ ኮሚሽኖችን ሁለት ጊዜ ያቋቋመ ሲሆን የመጀመሪያው የዋረን ኮሚሽን ሲባል ይህንን በዋናነት እንዲመራ የተደረገው ኬኔዲ በአንድ ወቅት ከስልጣን ያባረሩት የቀድሞው የሲ.አይ.ኤ. ዳይሬክተር ኤለን ዳላስ ሲሆን ጉዳዩን ምን ያህል ስላቅ እንዳደረገው ፍንትው አድርጎ ከማሳየቱም በላይ ከ15 ዓመት በኋላ የተቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን "ሃውስ ሴሌክት ኮሚቴ ኦን አሳሲኔሽን" ያወጣው ሪፖርት ከዋረን ኮሚሽን ሪፖርት የማይጣጣም ሲሆን ቢያንስ ከዋረን ኮሚሽን "እስዋልድ ብቻውን ገደላቸው" ከሚለው ቀልድ በተለየ በሴራ ሳይገደሉ እንዳልቀረ ይናገራል፤ ሴረኞችን ግን ለማጋለጥ የፈለገ አይመስልም እንጂ።የኬኔዲ አስገዳዮች ክንድ ዛሬም ድረስ የፈጠራ ታሪኮችን በማሰራጨትና በትክክል የማጣራቱ ስራ እንዳይተገበር እያደረጉ ዛሬ 50ኛ አመታቸው ላይ ደረሰን።የኬኔዲ ወንድም ሮበርት ኬኔዲ በጆን ኤፍ ኬኔዲ ዘመን "አተርኒ ጀነራል" በመሆን የፍትህ መስሪያ ቤቱን በበላይነት የመሩ ሲሆን በ1968 ዓ.ም. ለፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ውድድር እያደረጉ ሳለ ነበር በአንድ "ፍልስጤማዊ" ተገደሉ በሚል ተረት ጭንቅላታቸውን በጥይት ተመተው የተገደሉት። በህዝብ ዘንድ ካላቸው ተቀባይነት አንፃር ሮበርት ኬኔዲ ፕሬዚዳንት የመሆናቸው ዕድል የሰፋ በመሆኑ የወንድማቸውን ሞት በትክክል ያጣራሉ ከሚል ፍርሃት በወንድማቸው ገዳዮች ሴራ ሳይገደሉ እንዳልቀሩ ይገመታል።ቸር እንሰንብት!!!

# Reconciliation

**Yoseph Teklu Afewerk/ Fulda**

It is all of us, Ethiopians who must assume personal responsibility in bringing about a viable alternative, made more possible through reconciliation. A formal national reconciliation effort is critical, but must be preceded with interpersonal grassroots reconciliation in one`s own sphere of influence. This can be done by every person. Take responsibility yourself.

If you hear someone lumping all tigreans, Oromos, Amharas, Ogadeni or people from any other groups in to one box, do not remain silent. With civility, grace and conviction, confront what is being said. Do not condone it. This is a task for all of us.

As we become a people of moral convictions who accept and care about the humanity of others, we may `` get the leader we deserve,`` leaders who also have moral convictions and who accept and care about the humanity of others! Would that not be the beginning of a better Ethiopia? Let it begin with you!

May God empower Ethiopians to become ambassadors of reconciliation who, one by one , will bring healing and support leaders who will uphold truth, justice, the rule of law, equality and the respect of human and civil rights. God bless Ethiopia!

# The Devastating Human Right Violation in Ethiopia

**Desalegne Abebew& Yalemwork Meswaet /Gießen**

Ethiopian authorities are taking the members of opposition parties from their journey to unknown place where they are forced to drink alcohol, be beaten, be tortured and be raped. TPLF had killed people while they were moving in the car as it was caused by terrorist groups. They are torturing and mistreating political detainees to extract confession. Prisoners are being beaten and kicked during interrogation. Police investigators use illegal interrogation methods, keep inmates in poor detention conditions, and routinely deny them access to a lawyer The new Press Law and the Controversial Anti – Terrorism laws are some of the mechanical devices the dictatorial government muzzles opposition voices and fundamental human rights. These days two-third of the population is left to a complete destitution; and more than ever, a great deal of citizens are forced to leave the country as their security or livelihood is drastically under risk.

In the shadow of TPLF regime, many Ethiopian people have been abused inhumanly in the home country and at abroad. The Ethiopian government has become a slave for Arabic government by exporting his own citizen from its territory. TPLF is selling land of our family to Saudi lord; again they export our family to desert of Saudi to use them as a commodity for sex work. Lastly, the plan of TPLF is to inherit the fertile land of our family without any stingy person.

Our sisters living in Middle East and Arab countries are crying under the shackle of modern slavery; being denied their wage for the harsh

labor work they are subjected for. Some become victim of boiled oil by their employers and cry bearing life threatening burns and scars on their face and bodies. Many of young girls are being raped without their consent and become hopeless to get any legal protection or justice. Some have lost their life being thrown off high building and those who are lucky to survive are crying being disabled.

Many Ethiopians are left with no other option than leaving the country, crossing borders in tears. In the process of this forced migration, many Ethiopians cry for being victims of illegal and inhuman organ trade (trafficking) in Sinai and other desserts. Quite many cry falling in the fierce Jaw of beasts while crossing jungles. Others risk their life crossing dangerous sea and ocean waves on worn out boats under the shadow of death; and many of them cry while capsizing to be buried under sea bed or becoming live preys for sharks.

Currently, in Ethiopia the Amharas are crying as they are being displaced from place to place and treated as unwanted citizens in their own country. The same fate is hunting Oromo people and they cry in solitary. Scholars are crying as they are being sentenced to death for writing or telling the truth. Religious and sacred places have become war zones. Monks and nuns cry as they are being flogged and persecuted in Waldiba monastery. Who is not crying? The whole nation is crying; crying by the same cause: unlimited injustice and human right violations of EPRDF. We should stand up and unite together to bring sustainable and humane solutions for such a life threatening risks of the population in our country.

# Saudi Arabia Government: Stop Violence!

**Niguss Mengistu/Germany**

Today I want to send urgent message to all Ethiopian people concerning the brutal government of Saudi Arabia who tortured and killed to our innocent Brothers and Sisters. So to get in detail I have to say "Stop Violence…"

The Ethiopian people, who had a glorious history of honor and glory, today live in shame and humiliation mainly due to carelessness attention to those our Brothers and Sisters who died and suffering in Saudi Arabia. The most powerful statements that held the Saudi government responsible for crimes against humanity on the one hand the government in Ethiopia for lack of urgent interest to defend the rights and dignity of Ethiopians. Because of this and that Ethiopians can't tolerate till the whole world hear about our Brothers and Sisters pain So, for this reason our citizens in Addis Ababa, Ethiopia hundreds of people protesting against targeted attacks on Ethiopians in Saudi Arabia.

The purpose of these demonstrations is to demand the Saudi government to stop the violence, brutalization and killings of Ethiopian immigrants and have the Saudi re-

gime held accountable for the crimes it committed. But, we have seen in different social Medias when Ethiopian police used force to disperse hundreds of people protesting.

The Ethiopia government said the demonstration was illegal because they had not got permission from the appropriate office. Please allow me to l a u g h - ing….HAHAHAHAHAH…… that means, whatever happens the protester must wait until the cruel Saudi Arabia Government destroy to our all citizens and making suffer.

Also my questions are goes to the following **"**Almost blind human**"**

So like this devastating thing why those "Almost blind human" not take immediate actions like in every corner happens before but, we Ethiopians can't see until the rest of our Brothers and Sisters suffer by the inhuman government of Saudi Arabia, always we are here for you.


**Saudi Arabia Government - Full Responsible**




**Where Are They???**



**Other International Human Rights groups**



# Saudi Arabia: - Human-rights violations

**Murad Awel Hadju/Fulda**

The Saudis Typical abuses on Ethiopian migrants include long working hours, non-payment of salaries, refusal of permission to return home after completing contracts, refusal to transfer sponsorship and withholding of passports. Domestic workers who flee their employers can be arrested and charged with absconding. Some Ethiopian migrant workers experience physical abuse by their employers, but face enormous challenges in seeking legal remedies. Migrant workers who are able to take their employers to court find themselves embroiled in court cases that can last for years.

Countless other human-rights violations are occurring simultaneously in Saudi Arabia, of course, including against its large foreign-worker population. The Saudi government is infamous as a gross violator of human rights across the board. This will not, however, prevent the Saudi government, over the next three years, to sit in judgment of the human-rights record of the world. It is so amazing. The decision concretized the unfairness of the international body.

The Saudi government recently declined to take its seat on the U.N.'s Security Council. For the sake of decency, it should do the same for the Human Rights Council. But here it is not for the sake of decency, rather for the sake of their inhuman treatments of migrants as a whole. Saudi government should have to learn a lot from a countries like Germany, how people are respected any place. Long live to freedom of movement!

# Demonstration: A tool for real democracy

**Habtam Alemneh Belay/ Heusenstamm**

``Demonstration is a public meeting or March protesting against something or expressing views on a political issue. (A political rally or Protest) ``, Wikipedia

The present Ethiopian Prime Minister wants to limit the right of public meeting or demonstration. According to him, the repeated demonstrations in the country are useless and boring. Because of fear, the woyane regime will not allow demos in the future. The regime don`t wants to give a direct response for the questions of the people, that's why: - there are repeated

demos here and there. But the prime minister has not accepted the questions of the people.

I think the minister did not recognize the difference between the complaint and the response. If the Ethiopian government did not respond I think any one has the right to peaceful rally as long as the government is giving real answer not the one as TPLF giving. The difference of the Ethiopian government and others is the Ethiopian government did not hear its peoples where as the other respect the right of its peoples. God bless Ethiopia.

# Ending the silence!

**Michael Asefa, Nesibu/ Schweinfurt**

My mission is to lift the veil of silence and objective is to speak truth not only to the regime but also to those who have calculatedly chosen to disempower themselves by self-imposed silence. I insist that silently tolerating wrong over right is dead wrong. As it`s said, `` Nothing strengthens tyranny so much as silence. `` One cannot speak to tyrants in the language of silence; `` one must speak to tyrants, like those in Ethiopia.

Our silence to the tyrant EPRDF has made us to be marginalized and sidelined. If our silence is not broken, the tyrants will continue double crossing us, tricking us, lying to us, use and abuse us.

Even if the tyrants demonize us for questioning them and for demanding accountability and also for expressing ourselves, we are sentenced to hard labor in silence. Our innate value is determined not by the content of our character, individuality or humanity but the random chance of our ethnicity. We have no personality, nationality or humanity, only ethnicity.

That's why:- I insist all who claim to be supporters of democracy, freedom, human rights, and the rule of law to speak up and speak out. Never stand silent in the face of criminality, contrived ethnic animosity and the immorality of those who abuse power.

Well we freedom –loving Ethiopians have to break the silence to get the response for our appeals an authoritarian regime by opening new ideas and ways of communicating with people across age groups, ethnic, religious, gender and linguistic lines to maintain democracy with concomitant protection of human and civil rights, political pluralism, freedom from harassment, imprisonment and assassination for one`s convictions, free elections and an independent judiciary. God bless our home, Ethiopia!

# Oromos Are still EPRDF`s Target!

**Aster Gebremariam/ Bayreuth**

The Federal High Court of Ethiopia sentenced 21 Oromo Nationals (most of whom are university students) to as much as 2-8 years in prison on 7th August, 2013. The report I received indicates that all of them have spent about three years pending trials on alleged charges of collaborating with the opposition organization of Oromo Liberation Front with the intention of committing terrorist crimes. According to the information I obtained through different people, most of the defendants were very young Oromo students picked up at different times from different universities and colleges in the regional state of Oromia and other parts of the country.

I have learnt that most of the 21 Oromo defendants did not even have acquaintance of each other, let alone collectively committing terrorist crimes, as they were brought together from different universities in the country and met each other in the jail. According to some legal experts, the fact that the charges were mere fabrications aimed at imposing punishments intended for political intimidations has made it difficult for the accused to defend themselves.

However, by blatantly acting as a political tool of the ruling party, the court handed down the guilty verdict on the Oromo nationals without taking into consideration some evidences that the defendants attempted to present to defend themselves against the charges. Oromiya will prevail!

# ታላቅ የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ

## በጀርመን ለምትገኙ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች በሙሉ!

ዛሬም በወገኖቻችን ላይ የሚደርሰው መከራና ስቃይ አላቆመም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አስተማማኝ መፍትሄ እስከሚገኝ ድረስ ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ ድምጻችንን በማሰማት የዜግነት ግዴታችንን መወጣት የግድ ይላል በመሆኑም ከፍራንክፈርት ከሳዉዲ አረቢያ ኮንሱላት ጽ/ቤትና ከዛም በተጨማሪ

በሳዉዲ አረቢያ በግፍ ለተጨፈጨፉትና በየአገሩ ለሚንገላቱ ስደተኛ ወገኖቻችን በዋናነት ተጠያቂ የሆነዉን እንዲሁም በአዲስ አበባ ሳውዲ ኤምባሲ ለወገኖቻቸው ድምጽ ሊያሰሙ የወጡ ኢትዮጵያውያን ላይ ድብደባና እስር ያደረሰባቸውን የአምባገነኑን የወያኔ ሥርዓት ለመቃወም ፍራንክፈርት በሚገኘው ኮንሱላንት ፊት ለፊት ታላቅ የተቃዉሞ ሰልፍ ይደረጋል ስለዚህ በወገኖቻችን ላይ የተፈጸመው አሳዛኝና አረመኒያዊ ድርጊት የተሰማው ዜጋ ሁሉ አደባባይ በመውጣት ተቃውሞውን እንዲያሰማ ወገናዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን----------------!!!!!!!!!

**የሰልፉ ቀን፥ 03/12/2013 ቦታ፥ ዋና ባቡር ጣቢያ ሰዓት፥ 10፡00 /ጠዋት/**

**አዘጋጅ፥ በፍራንክፈርትና አካባቢው የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በሙሉ**

# ብሔራዊ ውርደት ይብቃ




ለበለጠ መረጃ፥ **01741986539 epcoug@yahoo.com**




# ጥላ መጽሔት ዘጠነኛ እትም

**ጥላ መጽሔት 2ኛ ዓመት ዘጠነኛ እትሟን ይዛ January 30/2014 ለንባብ ትበቃለች። ስለዚህ አዲስና ነባር ደንበኞቻችን በአዲሱ አድራሻችን ታገኙናላችሁ። በመጽሔታችን ላይ ያላችሁን አስተያየትና መልዕክቶች ሁሉ እስከ January 25/2014 ድረስ ልታደርሱን ትችላላችሁ።**

**ለበለጠ መረጃ የስልክ መስመራችንን መጠቀም ይቻላል።**

**WIR SIND IMMER FÜR SIE DA!**

**አዲሱ አድራሻችን**
**Mesfin Abraha**
**An der Obergeis 1**
**36251 Bad Hersfeld**
**E-Mail: tilamagazine@yahoo.de**
**Web-Site: tilamagazine.yolasite.com**
**Tel.No. 0152- 22195567**
**0176– 59384456, 0176-71668780**

**TILA MAGAZIN IST EURE MAGAZIN!**